

# ሐተታ ዘዘርአ ያዕቆብ

## በሚባል ስም የሚታወቀው

# የወርቄ የሕይወት ታሪክ

ትርጉም

በጌታቸው ኃይሌ

ኮሌጅቪል (ሚኒሶታ) ፳፻፮ ዓ.ም.

# *ሐተታ ዘዘርአ ያዕቆብ*

## በሚባል ስም የሚታወቀው

# የወርቄ የሕይወት ታሪክ

ትርጉም
በጌታቸው ኃይሌ

ኮሌጅቪል (ሚኒሶታ) ፳፻፯ ዓ.ም.

**ስለተርጓሚው መብት**

**ለትርፍ እስካልሆነ ድረስ፣ ይህን መጽሐፍ ይዘቱን ሳይለውጡ መገልበጥ ማራባትም ሆነ ማሳተም ይቻላል**

**ሽፋን**

**የፊት፡ ጐንደር፣ የአፄ ፋሲለደስን መታጠቢያ አጥር አቅፈው የበቀሉ ዛፎች ስር፡**

**የኋላ፡ አክሱም፣ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የተሠራው የጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያን**

አቶ ኣምሃ ኣስፋው በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ያመለጡትን የፊደል ግድፈቶችና የአገላለጽ ጐደለቶች አርሞ፥ ለመጽሐፉ ቅርጽ ሰጥቶ፥ በፎቶግራፍ ስላጐናጸፈው ከልቤ አመሰግነዋለሁ።

# መዘክር

**ለአቶ አሰፋ ገብረ ማርያም ተሰማ**

***ሐተታ ዘዘርአ ያዕቆብን*** **ከግዕዝ ወደ አማርኛ እንድተረጒመው የገፋፉኝ አቶ አሰፋ ገብረ ማርያም ስለሆነ መታሰቢያው ይሁንልኝ።**

# *ሐተታ ዘዘርአ ያዕቆብ*

# በሚባል ስም የሚታወቀው የወርቄ የሕይወት ታሪክ

## *መቅድም*

አንድ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ (Padre Giusto da Urbino) የሚባል የካቶሊክ ሚሽኔሪ ደብረ ታቦር (ደምቢያ) ላይ ሆኖ በፌብሩዋሪ 1853 ዓ.እ.(=1844ዓ.ም.) የአንድ የግዕዝ ድርሰት ሁለት ቅጂዎች በዚያን ጊዜ ፓሪስ ለሚኖረው አንቷን ዳ'አባዲ (Antoine d'Abbadie) ይልክለታል። አንቷን ዳ’አባዲ በዘመነ መሳፍንት ኢትዮጵያ መጥቶ ዛሬ ከታላቁ የፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ካሉት የግዕዝ መጻሕፍት አብዛኞቹን ሰብስቦ ያመጣ ተመራማሪ ነበር። አንቷን ዳ’አባዲ እነዚህን ሁለት ቅጂዎችም በዚያው በታላቁ ቤተ መጻሕፍት ከትቷቸው፥ አንደኛው በስሙና በቊጥር፥ D'Abbadie 215፥ ሁለተኛው D'Abbadie 234 በመባል ይታወቃሉ። **“ሐተታ ዘዘርአ ያዕቆብ”** የሚባለውን የኢትዮጵያ ጥናት ሊቃውንትን ያጨቃጨቀውን የወርቄን የፍልስፍና ትችት የያዙ እነዚህ ሁለት ቅጂዎች ናቸው።

ጭቅጭቁ ምን እንደሆን ያልሰማ እንዳለ፥ በአጭሩ እንዲህ ነው፤ ይህ ድርሰት በዓሥራ ሰባተኛው ምእት ዓመት የኖረ ዘርአ ያዕቆብ የሚባል ኢትዮጵያዊ የደረሰው አይደለም፤ ፓድሬ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ (Padre Giusto da Urbino) ሚሲዮናዊ ስለሆነ ማንነቱ እንዳይታወቅ “ዘርአ ያዕቆብ” የሚል የብዕር ስም አውጥቶ የደረሰው ነው የሚል ነው። ቅጂዎቹን ሊያያቸውና ሊመረምራቸው የሚፈልግ መታወቂያቸውን ጠቅሶ ፎቶግራፉቸው ከፓሪስ እንዲላክለት መጠየቅ ይችላል። ጭቅጭቁ የተካሄደባቸውን ምንጮች ከዚህ ጽሑፍ መጨረሻ ዘርዝሬያቸዋለሁ።

ከሁለቱ ቅጂዎች D'Abbadie 215 ወልደ ሕይወት የሚባለው የወርቄ (የዘርአ ያዕቆብ) ደቀ መዝሙር አፄ ዮሐንስ/አእላፍ ሰገድ ሲነግሥ (1660 ዓ.ም.) ካዘጋጀው ላይ የተቀዳ ነው። ዋናው አሁን የት እንዳለ አይታወቅም። ሌላው፥ D'Abbadie 234፥ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ አሳጥሮ በፈረንጅ እጁ የቀዳው ነው። ተመራምሬ እንደደረስኩበት፥ እነዚህ ሁለት ቅጂዎች የተቀዱት በ1851 ዓ.እ. (=1844 ዓ.ም.) ነው።

*ዳ ኡርቢኖ ሲቀዳ እያሳጠረ ብቻ ሳይሆን፥ በግዕዝ ችሎታው ተማምኖ፥ መታረም የማያስፈልጋቸውንም ቃላትና ዐረፍተ ነገሮች ሳይቀሩ "እያረመ"፥ ደራሲውን በዓለም ስሙ ወርቄ በማለት ፈንታ፥ በክርስትና ስሙ ዘርአ ያዕቆብ እያለ፥ ወርቄ ለድርሰቱ ያልሰጠውን ስም አውጥቶለት* ***"ሐተታ ዘዘርአ ያዕቆብ"*** *እያለ ነው።*

*ከዚያም አልፎ ተርፎ፥ ድርሰቱ በክርስቲያኖች ዓይን ሲታይ ህርጥቅና* (heresy) *ስለሆነ፥ "እንዳልታወቅ ዘርአ ያዕቆብ በሚል በብዕር ስም የጻፍኩት እኔ ነኝ" ሳይል አልቀረም። የጻፈው ማስታወሻ ተገኘ ተብሎ፥ በካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ መሪነት ድርሰቱ ከዘርአ ያዕቆብ (ከወርቄ ማለት ይሻላል) ተወስዶ ለጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ተሰጠ። ሌሎች ተመራማሪዎችም፥ በተለየም ኦይገን ሚትቮኽ* (Eugen Mittwoch) *የኮንቲ ሮሲኒን ፍርድ አጸኑ። ፓድሬው በወርቄና በድርሰቱ ላይ ያደረሰውን በደል እስከዛሬ ከሊቃውንቱ አእምሮ መፋቅ አልተቻለም።*

*የኮንቲ ሮሲኒ አቋም ኢትዮጵያውያንን አስቆጣ። የዘርአ ያዕቆብን ስም ሰምተው የማያውቁ ሁሉ ፈላስፋ ነው ስለተባለ ብቻ ኢትዮጵያዊ እንደነበረ መሰከሩለት። ኦይገን ሚትቮኽ ዘርአ ያዕቆብንና ፍልስፍናውን የኢትዮጵያ ሊቃውንት ያውቁት እንደሆን፥ ካወቁትም አስተያየታቸው ምን እንደሆነ እንዲነግሩት ካስጠየቃቸው ሰዎች አንዱ የአማርኛ መዝገበ ቃላት የጻፉት አለቃ ደስታ ተክለ ወልድ ነበሩ። ካቶሊካዊው አለቃ ደስታ፥ "ሰውየውም ድርሰቱም በኢትዮጵያ አይታወቅም" ብለው እቅጩን መልስ በመስጠት ፈንታ፥ የግል አስተያየታቸውን የጠየቃቸው ይመስል፥ አንድ ሰው አውሷቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ለአንዳፍታ ያዩትን "ሐተታ ዘዘርአ ያዕቆብ" እየተነተኑና መልሰው እየቀዱለት እንዲህ ሲሉ ጻፉለት፤*

> *ዘርአ ያዕቆብ የአክሱም ሰው ነው፤ ሁለተኛ ስሙ ወርቄ ይባላል። እንደ ኢትዮጵያ ትምሕርት እጅግ ሊቅ ነበር። ሰውየው ጠባየ መልካም ኖሯልና ከዚያም ከዚያም ሲል ላቲን ተምሯል። የነበረው ባጼ ሱስንዮስ ጊዜ ነውና በዚያን ጊዜ አባ አልፎንስ የሚባሉ ጳጳስ ዠዙዊት ካቶሊካዊ መጥተው ንጉሡ ካቶሊክ ስለሆኑ በኢትዮጵያ ብዙ የሃይማኖት ጭቅጭቅ ሆኖ ስለ ነበረ፥ ዘርዓ ያዕቆብ የመጽሐፍ መምሕር የሃይማኖት ዓይነተኛ ሰው ኦርቶዶክሳዊ ነበርና ንጉሡን ፈርቶ ፪ት ዓመት ካንድ ዋሻ ተደብቆ ነበር። በዚያ ሳለ በሀሳብ ብዛትና በብስጭት ስለ ክርስቶስ በሚሆነው ክርክር ሃይማኖቱን ለወጠ። ሐሳቡና አጻጻፉ ሁሉ ልክ እንደ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ነው። . . . ምንም ከመጽሐፉና ካነጋገሩ ሮማዊ (ፈረንጅ) ነው ለማለት የሚያግዝ ነገር አላየሁበትም። ሰውዬው ቢሆን*

> ዕውቀቱ ሰፊ ነበር፤ ነገር ግን ስለ ክርስቶስ ሥጋዌ የመድኃኒታችንን ነገር ቸል በማለቱ አናመሰግነውም። ሮማዊ ነው የሚሉትም መርማሪዎች፥ እንዲህ ያለ ሊቅ በኢትዮጵያ አይገኝም በማለት ነው እንጂ እርሱ ግን ፍጹም ኢትዮጵያዊ እንደሆነ ካጻጻፉና ከመጽሐፉ ይታወቃል። እኔም መጽሐፉን [ሐተታ ዘዘርአ ያዕቆብን] ጥቂት እንደመረመርኩት ወዲያው ባለቤቱ ወሰደው። ጤና ይስጥዎ።

አለቃ ደስታ ሚትሮ'ኽ የሚያውቀውን እንጂ፥ ሊያውቅ የፈለገውን መልስ አልሰጡትም፤ ግን ሊቃውንቱ ዘርአ ያዕቆብን የማያውቁት መሆኑን ካነጋገራቸው አግኝቶታል።

የኮንቲ ሮሲኒ አቋም ኢትዮጵያውያንን አስቆጣ። ለምን ይኸን አቋም እንደያዘ ሌላ ትርጉም መስጠትም አመጡ። እንደማየው፥ የኮንቲ ሮሲኒ ምርምር ተንኮል የተሞላበት አይደለም። የዳ ኡርቢኖን ማስታወሻ ባላየውም፥ ኮንቲ ሮሲኒ ፈልጎ ማግኘቱ በምርምር ረገድ የሚያስመሰግነው ነው። ኮንቲ ሮሲኒን የተቃወሙ ኢትዮጵያውያን "ድርሰቱ የአንድ ኢትዮጵያዊ ነው" ሲሉ የሚሰጡት ማስረጃ በብሔርተኝነት ስሜት የታጀበ ስለሆነ ከልብ ስለማይገባ፥ ጉዳዩን ትቸው ነበረ።

ግን ወይዘሮ ሉአም ተስፋ ልደት ለማስትሬት ምርቃት የጻፈችውን ጥልቀት ያለውን ድርሰት ሳነብ፥ ሁለቱን ቅጂዎች ከፓሪስ አስመጥቼ በቅርብ እንዳጠናቸው ገፋፋኝ። አጥንቼ በእንግሊዝኛ ያዘጋጀሁትን ከሌላ ቦታ አሳትመዋለሁ። አሁን ድርሰቱን አቶ አሰፋ ገብረ ማርያም ተሰማ ወደአማርኛ እንድተረጉመው ስለገፋፋኝና ስለተረጐምኩት፥ ከዚህ አጭር መቅድም ጋር ለአቶአሰፋ መታሰቢያ አድርጌ ለሕዝብ ላበረክተው ወሰንኩ። ስለደራሲው ማንነት (በዓሥራ ሰባተኛው መቶ ዓመት የኖረ ኢትዮጵያዊ እንጂ፥ በዓሥራ ዘጠነኛው መቶ ዓመት የኖረ ኢጣሊያዊ እንዳይደለ) የምሰጠው ፥ በተለየም ከዘመኑ የኢትዮጵያ ታሪክና ባሕረ ሐሳብ ተነሥቼ፥ የማቀርበው ማስረጃ የተመራማሪዎችን አቋም እንደሚለውጥ ተስፋ አደርጋለሁ። (እዚህም በአጭሩ እገልጸዋለሁ።)

ከስሩ ልጀምርና፥ ከላይ እንደጠቆምኩት፥ ደራሲው ለድርሰቱ ርእስ ወይም ስም አልሰጠውም። **ሐተታ፡ ዘዘርአ፡ ያዕቆብ ፡** (የዘርአ ያዕቆብ ትችት) የሚል ርእስ የሰጠው ቅጂዎቹን ወደፓሪስ የላከው ፓድሬ ዳ ኡርቢኖ ነው። ደራሲው ወርቄ ግን፥ ድርሰቱን "(እግዚአብሔር) ለነፍሴ ምን ያህል እንደሠራላት ልንገራችሁ" ብሎ ብቻ ነው

የጀመረው። እውነትም ያነበበው ሁሉ እንደሚያየው፥ ሰውየው የጻፈው በግል ሕይወቱ የደረሰበትንና አስተሳሰቡን የለወጠበትን አጋጣሚ አንጻፍታ ሊያወጋን አስቦ ነው። ግን አስተሳሰቡ ለራሱም ሆነ ለዘመዶቹ አደገኛ ስለሆነ የጻፈው የራሱንና የትውልድ ሀገሩን ስም እየለወጠ ይመስለኛል። ምክንያቴን በግልጽ አሳያለሁ።

ደራሲው ስለራሱ እንደሚነግረን፥ የተወለደው ነሐሴ 25 ቀን 1592 ዓ.ም. አክሱም አካባቢ ከአንድ የገበሬ ቤተ ሰብ ነው። ሲወለድ **ወርቄ** ተባለ፤ ክርስትና ሲነሣ፥ **ዘርአ ያዕቆብ** ተባለ። በባህላችን መሠረት፥ ሰው የሚጠራው በዓለም ስሙ እንጂ በክርስትና ስሙ አይደለም። ራሱም የሚለው ይኸንኑ ነው፤ "ክርስትና ስነሣ ዘርአ ያዕቆብ ተባልኩ፤ ሰዎች ግን ወርቄ ነው የሚሉኝ" ብሎ ተናግሯል። በክርስትና ስሙ እንዲታወቅ ያደረገው ፓድሬ ዳ ኡርቢኖ ነው ብያለሁ። ለከፍተኛ ትምህርት ሲደርስ፥ ዘመኑ ካቶሊኮች የገነኑበት ዘመን ነበረና፥መጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ ከካቶሊኮች ዘንድ፥ በኋላ ደግሞ ከኢትዮጵያውያን መምህራን ዘንድ እንደተማረ ይነግረናል። ወርቄ ትምህርቱን ጨርሶ አስተማሪ ሲሆን፥ ችግር ተፈጠረበት፤ ከተማረው ትምህርት የትኛውን ያስተምር? የካቶሊኮቹን ወይስ የኛን? የኛማ ድሮውንም ከልቡ አልገባም ነበር። "(የኢትዮጵያ መምህራን) ትርጓሜያቸው ብዙ ጊዜ ከኅሊናዬ ጋራ አይስማማም ነበረ" ይለናል። መፍትሔውን እንዲህ ሲል ያመጣዋል፤

> መጻሕፍቱን ስተረጒም "ፈረንጆች እንዲህ፥ እንዲህ ይላሉ፤ ግብጻውያን እንዲህ፥ እንዲህ ይላሉ" እላለሁ፤ "እኛ ጥሩዎች ስንሆን ሁሉም ጥሩ ይሆናል" እላለሁ እንጂ "ይኸኛው ደኅና ነው፤ ይኸኛው መጥፎ ነው" አልልም። በዚህም ምክንያት ሁሉም ጠሉኝ፤ ምክንያቱም ለግብጻውያኑ ፈረንጅ ስመስላቸው ለፈረንጆቹ ግብጻዊ እመስላቸው ነበረ። (ሰዎች) ብዙ ጊዜ ከንጉሡ (ከአፄ ሱስንዮስ) ዘንድ የውሸት ክስ አቀረቡብኝ።

የትውልድ ሀገሩ አክሱም አካባቢ መሆን የሚያጠራጥረው እዚህ ላይ ይጀምራል። አንደኛ፥ ጥንቁቁ ወርቄ የመንደሩን ስም አልነገረንም፤ ሁለተኛ፥ እሱ የሚያስተምረው አክሱም ከሆነ፥ እንዴት ነው ጠላቶቹ ንጉሡ አፄ ሱስንዮስ (1600-1625) አለበት ደንቀዝ (ደምቢያ) ድረስ ብዙ ጊዜ እየተመላለሱ የውሸት ክስ የሚያቀርቡበት? አክሱምና ደንቀዝ ሰዉ ጧት ማታ የሚመላለስባቸው ጎረቤት ከተሞቶች አይደሉም። በካቶሊኮቹ ምክንያት የሃይማኖት ጭቅጭቅ የተነሣው በሁሉም ቦታ ቢሆንም፥ የተፋፋመው እዚያው እደምቢያ ስለሆነ፥

እሱም ከሳሾቹም የደምቢያ ሰዎች ሳይሆኑ አይቀሩም። ተከሶ ከንጉሡ ፊት ሲቀርብ፥ ንጉሡ ገንዘብ (ወርቅ) ሰጥቶ አሰናበተው። በፈረንጆቹ ሃይማኖት ውብነት ንጉሡና ወርቄ እኩል ቢረኩበት መሆን አለበት።

ለሁለተኛ ጊዜ በተንኮል ተከሶ ከንጉሡ ፊት የሚያቀርቡት ዘበኞች እንደሚመጡ ቀደም ብሎ ሲያውቅ፥ ከአንድ ዋሻ ገብቶ ተደበቀ። ዘመዶቹ የቤተ መንግሥት ባለሟሎች፥ እሱም ያስተምር የነበረው እዚያው አካባቢ ካልሆነ፥ አክሱም ሆኖ፥ ከደምቢያ (ከበጌምድር) ወታደሮች ሊያስሩት መምጣታቸውን አስቀድሞ ሊያውቅ ይችል አይመስለኝም።

ሌላም የማይታለፍ ደጋፊ ነጥብ አለ፤ የሱስንዮስን አልጋ ልጁ ፋሲለደስ (1625-1660) ሲወርስ፥ ወርቄ ከተደበቀበት ወጥቶ ወደ እንፍራዝ (ደምቢያ ውስጥ) ሄዶ ተቀመጠ። አሁን ደግሞ ያው ጠላቱ ወልደ ዮሐንስ የካቶሊኮችን ሃይማኖት ይደግፋል ብሎ አዲሱ ንጉሥ ፋሲለደስ ላይ ከሰሰው። ወልደ ዮሐንስ በኋላ በደምቢያ ገዳማት ላይ መሾሙንም ወርቄ ይነግረናል። በባህላችን መሠረት ነገሥታቱ ሰው የሚሾሙት አብዛኛውን ጊዜ በትውልድ ሀገሩ ላይ ነው። ስለዚህ ወርቄና ጠላቱ ወልደ ዮሐንስ ሁለቱም ያንድ አካባቢ (የደምቢያ) ሰዎች መሆን አለባቸው። ወርቄ/ዘርአ ያዕቆብ በጌምድሬ፥ በዛሬው አነጋገር፥ ጎንደሬ ነበር።

ለማንኛውም፥ ወርቄ/ዘርአ ያዕቆብ የፍልስፍና ምርምሩን የጀመረው እዚህ ዋሻ ውስጥ ነው። ይዞት የሸሸውን ዳዊቱን ከደገመ በኋላ ሥራ ፈትቶ ቁጭ ሲል፥ ጥልቅ ጥያቄዎችን ማንሣት መጣል ጀመረ። ሲርበው ወጣ ብሎ ይለምናል። ወርቅም ስለነበረው ወደገበያም ብቅ ይል ነበር። ንጉሥ ሱስንዮስ እስኪሞት ድረስ እዚያው ቆየ። የፍልስፍና አስተሳሰብ የቀሰቀሰበት የተማረው የኦርቶዶክሱና የካቶሊኩ ሃይማኖት አለመስማማትና ሥራ ፈትነቱ ነበር። ከሁለቱ ሃይማኖቶች ትክክለኛው የትኛው ነው? ከማለት አልፎ፥ **ለመሆኑ ፈጣሪ፥ እግዚአብሔር፥ አለ ወይ?** ከሚል ጥርጣሬ ገባ። የምርምሩ ውጤት በሁለት ቅጂ ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ተገኙ።

“በኢትዮጵያ ዘርአ ያዕቆብ የሚባል አንድ ፈላስፋ ወጣ” የተባለው በዚህ ምክንያት ነው። የኢትዮጵያ መምህራን የእግዚአብሔርን መኖር ሲያጠናክሩ እንጂ፥ ሲጠራጠሩ ታይተው አይታወቁም። ድርሰቱን ኤኖ ሊትማን (Enno Littmann) ከD'Abbadie 215 ላይ ቀድቶ

በአድንቆት አሳተመው፤ ለD'Abbadie 234 ግን ዋጋ አልሰጠውም፤ አለመስጠቱ ጉዳት ነበረ፤ በኋላ ቦሪስ ቱራኢየቭ (Boris Turayev) ሁለቱን ቅጂዎች አመሳክሮ አሳተማቸው።

ከቱራኢየቭና ከሚትቮኽ ኅትመቶች በኋላ የዘርአ ያዕቆብ (የወርቄ) ኢትዮጵያዊነት በምዕራቡ ምሁራን ዘንድ አቆመ። ክላውድ ሳምነር (Claude Sumner) አቅም ስለሚያንሰው ዘርአ ያዕቆብን ኢትዮጵያዊ ለማድረግ ያደረገው ጥረት ምናልባት ከሀገር ወዳዱ ሕዝብና ከካቶሊክ እምነት ተከታዮች ዘንድ ካልሆነ በቀር ከሊቃውንቱ መካከል አድናቂ አላተረፈለትም። "ዘርአ ያዕቆብ የኛ ፈላስፋ ነው" ከሚሉት ኢትዮጵያውያን መካከል የኦርቶዶክስ ተከታዮችም አሉባቸው። ሰውየው ግን ሃይማኖትን ሁሉ ቢያጣጥልም፥ የካቶሊክን ሃይማኖትና ተከታዮቹን ከኦርቶዶክስ ሃይማኖትና ከተከታዮቹ አብልጦ ያከብራል፤ ኦርቶዶክሶችን ላስፈጀ ለንጉሥ ሱስንዮስ ያለው አክብሮትና የኦርቶዶክስን ሃይማኖት መልሶ ላቋቋመውና ግራኝ ያቃጠላትን የአክሱም ቤተ ክርስቲያን አሳምሮ ላሳደሰው ለንጉሥ ፋሲለደስ ያለው ንቀት እንደሰማይና እንደምድር ይራራቃሉ። ከአንድ ሺ አንድ ሌሊት (*One Thousand and One Nights*) የሰማውን ተረት እየወሰደ፥ "ከሴቶቹ ጋራ ዝሙት ከሠራ በኋላ ገደላቸው" ብሎ ጻፈበት።

ሆኖም፥ በሚታመን ማስረጃ የሚከራከርለት አጥቶ ነው እንጂ፥ ወርቄ (ዘርአ ያዕቆብ) ኢትዮጵያዊ መሆኑ አያጠራጥርም፤ ሌሎችም እንዳመለከቱት፥ የጸሎቱ መጽሐፍ እንደማናቸውም ኢትዮጵያዊ ካህን መዝሙረ ዳዊት ነው። ጥቅሶቹ እንደሚያሳዩት፥ ዳዊቱን በቃሉ ያውቀዋል። ምዕራባውያን (እነ ፓድሬ ዳ ኡርቢኖ) ዕለታዊ ጸሎታቸውን የሚያደርሱት ባዘጋጁት የጸሎት መጽሐፍ እንጂ፥ እንደኛ ሕዝበ ክርስቲያን ዳዊት በማንበብ አይደለም። የዘርአ ያዕቆብን ኢትዮጵያዊነት ለመመስከር፥ ከታሪክና ከባሕረ ሐሳብ ያገኘሁትን (ሌሎች ተመራማሪዎች ልብ ያላሉትን) ማስረጃዬንም ዝቅ ብዬ አቀርባለሁ።

ፍልስፍናው በመሠረቱ የሱ መሆኑን ግን በሁለት ምክንያቶች እጠራጠራለሁ። አንደኛ፥ ተፈላስፎ የእግዚአብሔርን መኖር ያመነው፥ የሚያየው **ፍጡር ሁሉ ያለፈጣሪ አይፈጠርም** ከማለት ተነሥቶ ነው። ይኸንን ከቅዱስ ቶማስ አኩይናስ (Thomas Aquinas, 1225-1274) ጀምሮ በካቶሊኮች ዘንድ የገነነ "ምክንያትና ውጤቱ" (The law of causality) አስተሳሰብ ወርቄ የካቶሊኮቹ ተማሪ በነበረበት ጊዜ አልሰማውም ማለት ያስቸግረኛል።

ሁለተኛ፥ ከሁሉም የሚገርመው “የኮከቦችን ቍጥር፥ ርቀታቸውን፥ ስለርቀታቸው ትናንሽ የሚመስሉን ትልቅነታቸውን ማን ያውቃል?” ማለቱ ነው። ኮከቦች ትናንሽ የሚመስሉት በርቀታቸው ምክንያት መሆኑን በቴለስኮፕ እንጂ በመፈላሰፍ የሚደረስበት አይደለም። ይኸንንም የካቶሊኮቹ ተማሪ በነበረበት ጊዜ ከእነሱ አፍ አልሰማውም ማለት ያዳግተኛል። ዋናው ቁም ነገር ግን ዘርአ ያዕቆብ የሚነግሩትን የሚሰማ ሰፌ ጆሮ፥ የሰማውን የሚመረምም ትልቅ አእምሮ የነበረው ሰው መሆኑ ነው። የድርሰቱ ውበት ማንበብ የጀመረ ሳይጨርስ የማይለቀው ነው። አማርኛዬ የግዕዙን ውበት እንዳስተጋባ ተስፋ አለኝ።

“ዘርአ ያዕቆብ ኢትዮጵያዊ መሆኑ አያጠራጥርም” ያልኩበትን የማያፈናፍኑ ተጨማሪ ማስረጃዎቼን ላምጣና መቅድሜን ልደምድም። የማስረጃዎቼ ውጤት ሁለት ጥቃቅን ስሕተቶች የወለዱት አንድ ዓቢይ እውነት ሊባል ይችላል። አንዱ ታሪክን፥ ሁለተኛው ባሕረ ሐሳብን ይመለከታል። የምዕራባውያን ምርምር የደመደመው “ዳ ኡርቢኖ” እና “ዘርአ ያዕቆብ” የአንድ ሰው (የፓድሬ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ) እውነተኛና የብዕር ስሞች ናቸው፤ “ዘርአ ያዕቆብ” የሚባል ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ የለም ብሎ ነው። (“ዘርአ ያዕቆብ” የፓድሬ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ለራሱ ያወጣው የብዕር ስም ነው።)

የማቀርባቸው የታሪክ እና የባሕረ ሐሳብ ማስረጃዎች የሚመሰክሩት “ዘርአ ያዕቆብ” እና “ፓድሬ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ” በተለያየ ዘመን የኖሩ የሁለት ሰዎች ስሞች መሆናቸውን ነው።

ታሪኩ፤ “ፋሲል” እና “ፋሲለደስ” አንድ ናቸው። “ፋሲል” ኋላ የመጣ ነው፤መሆን ያለበት “ፋሲለደስ” ነው። ስገምተው፥ በዘርአ ያዕቆብ ጊዜ “ፋሲል” የሚለው አጭር ስም አይታወቅም ነበር። የሐተታ ደራሲ የጻፈውም “ወነግሠ ወልዱ ፋሲለደስ” (ልጁ ፋሲለደስ ነገሠ) ብሎ ነበር። ግን የD'Abbadie 215 ቀጂ፥ ምንም ጎንደሬ ቢሆም፥ ፋሲለደስ የሚባል ሰማዕት (ቅዱስ ፋሲለደስ) እንጂ ንጉሥ እንዳለ ልብ አላለውም ነበር። እሱ የሚያውቀው ንጉሥ ስሙ ፋሲል ነው። ስለዚህ፥ ይህ ሰው ዘርአ ያዕቆብ በዓሥራ ሰባተኛው ምእት ዓመት “ወነግሠ ወልዱ ፋሲለደስ” ያለውን ሲቀዳ፥ እንዳለ በመቅዳት ፈንታ፥ በራሱ ዘመን፥ በዓሥራ ዘጠነኛው ምእት ዓመት፥ አነጋገር ስሕተት መስሎት፥ “ወነግሠ ወልደ ፋሲለደስ” (“ወልደ ፋሲለደስ ነገሠ”) ብሎ ለወጠው። (ወልደ ፋሲለደስ ማለት ወልደ ጊዮርጊስ እንደማለት ነው።) ይህ ስሕተት ዘርአ ያዕቆብና ዳ ኡርቢኖ የሚባሉ

በተለያየ ዘመን የኖሩ ሁለት ሰዎች መሆናቸውን ያመለክታል። ይህ ከታሪክ ረገድ ነው።

በባሕረ ሐሳብ ረገድ ስናየው፥ በሁለቱ ቅጂዎች ውስጥ እነዚህ ሁለት ዘመኖች (ዘርአ ያዕቆብ የኖረበት ዓሥራ ሰባተኛው ምእት ዓመትና ዳ ኡርቢኖ የኖረበት ዓሥራ ዘጠነኛው ምእት ዓመት) በባሕረ ሐሳቡ አማካይነት ቁልጭ ብለው ይታያሉ። አንድ ቦታ ላይ D'Abbadie 215 "አመ፡ ፲፩ለጥቅምት፡ በዕለተ፡ ሰኑይ፡ እምልደተ፡ ክርስቶስ፡ ፲፻ወ፮፻ወ፴ወ፩" (ጥቅምት 11 ቀን፥ ሰኞ ዕለት ከክርስቶስ ልደት በ1631 [ዓመት]) የሚል አለ። እዚህ ላይ የ ዳ ኡርቢኖ ቅጂ (D'Abbadie 234) ጥቅምት 10 ቀን፥ ሰኞ ዕለት ከክርስቶስ ልደት በ1631 [ዓመት]) ይላል። መጀመሪያ "ሰኞ"ን ወደ "ማክሰኞ" ሊለውጥ እንዳሰበ እርማቱ ያስታውቃል። "ማክሰኞ" ብሎ የጻፈውን ሰርዞና "ሰኞ"ን ከቦታው መልሶ፥ (ጥቅምት 11ን ጥቅምት 10 አድርጎታል። ዳ ኡርቢኖን ግራ የገባው፥ በእሱ ዘመን ጥቅምት 11 ቀንና ሰኞ አለመገጣጠማቸው ነው። ድርሰቱ በተጻፈበት 1631ዓ.ም. እንደሚገጣጠሙ ልብ ስላላለው፥ ሊያርመው ተነሣ። ግን ስሕተት የሚፈጠረው ቍጥር ሲቀዳ መሆኑን በመገመትና በ1844 (1851ዓ.እ.) ሰኞና ጥቅምት 10 ሲገጣጠሙ በማየት ከዕለቱ ይልቅ ቍጥሩን ከ11 ወደ 10 ለወጠው። ቅጂዎቹን በ1853 ዓ.እ. ከመላኩ ከሁለት ዓመት በፊት ማለት ነው። በዚህ አስተሳሰብ፥ ዳ ኡርቢኖ በ1631 ዓ.ም. የተደረሰውን የዘርአ ያዕቆብን ድርሰት ያስቀዳው፥ የራሱንም አጭር ቅጂ ያዘጋጀው፥ በ1851 ዓ.እ. ነው። ድርሰቱ ዳ ኡርቢኖ በብዕር ስም የጻፈው ቢሆን ኖሮ፥ ይኸን የሚያህል ትልቅ ስሕተት አይታይበትም ነበር።

**ማስታወሻ፤**

1. ትርጕሙ ውስጥ በ (B) የተመለከተው D'Abbadie 215 እና የቅጠሉ ገጽ ነው።
2. የጠቀስኳቸውን ደራሲዎችና ድርሰቶቻቸውን ከትርጕሜ መጨረሻ ላይ በዋቢ ምንጭ ስር አቅርቤያቸዋለሁ።

ጌታቸው ኃይሌ

የካቲት 15 ቀን 2006 ዓ. ም. (February 22, 2014)

# *ሐተታ ዘዘርአ ያዕቆብ* በሚባል ስም የሚታወቀው የወርቄ የሕይወር ታሪክ

## [ክፍል አንድ]

(B, 1r) (በእውነተኛነት ብቸኛ በሆነው በእግዚአብሔር ስም የዘርአ ያዕቆብን ታሪክ[1] ከጥበቡና ከትችቱ ጋራ እሱ ራሱ (እንዲህ) ሲል የደረሰውን እጽፋለሁ። "እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሁሉ፥ ኑ ስሙኝ፤ (እግዚአብሔር) ለነፍሴ ምን ያህል እንደሠራላት ልንገራችሁ።"[2] እነሆ እጀምራለሁ።

ሁሉን በፈጠረ፥ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም በሆነ፥[3] ሁሉን በያዘ፥[4] የሕይወት ሁሉና የጥበብ ሁሉ ምንጭ በሆነ፥ በእግዚአብሔር ስም ፥ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ከደረሰብኝ በጥቂቱ እጽፋለሁ። "ነፍሴ በእግዚአብሔር ትከብራለች፤ የዋሃን ይስሙና ይደሰቱ።"[5] ምክንያቱም፥ "እግዚአብሔርን ፈልጌው መልሶልኛልና። አሁንም እናንተም ወደሱ ቅረቡ፤ ያበራላችኋል። ፊታችሁ አያፍርም።"[6] "እግዚአብሔርን ከኔ ጋራ ከፍ ከፍ አድርጉት፤ ስሙንም አብረን ከፍ ከፍ እናድርግ።"[7]

ጥንተ ትውልዴ ከአክሱም ካህናት ነው። ሆኖም እኔ የተወለድኩት በአክሱም አካባቢ ከአንድ ደኻ ገበሬ፥ በነሐሴ 25 ቀን፥ በያዕቆብ መንግሥት በ3ተኛው ዓመት፥ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ1592 ዓመት

---

[1] ገድል፡
[2] መዝ. 65፥ ቍ. 16.
[3] ራእይ ም. 1፥ ቍ. 17.
[4] መጽሐፈ ቅዳሴ፡
[5] መዝ. 33፥ ቍ. 2.
[6] መዝ. 33፥ ቍ. 4-5.
[7] መዝ. 33፥ ቍ. 3.

ነው። ክርስትና (B, 1v) ስነሣ ዘርአ ያዕቆብ ተባልኩ፤ ሰዎች ግን ወርቄ ነው የሚሉኝ።

ባደግሁ ጊዜ እንድማር አባቴ ትምህርት ቤት አስገባኝ። ዳዊት ስደግም አስተማሪዬ ላባቴ፥ "ይኽ ሕፃን ልጅህ ልበ ብሩህ ነው። ትምህርትም አይሰለቸውም። (ከፍተኛ) ትምህርት ቤት ብታስገባው ሊቅና መምህር ይሆናል" አለው።

አባቴ ይኽንን ሰምቶ ዜማ እንድማር (ዜማ ትምህርት ቤት) አስገባኝ። ግን ድምፄ ጥሩ አይደለም፤ ጉሮሮዬም ጎርናና ነው። በዚህም ምክንያት ለጓደኞቼ ሣቅና ስላቅ ሆንኳቸው። እዚያ 3 ወር ቆየሁ፤ ከዚያ በኋላ በልቤ እያዘንኩ ተነሥቼ ቅኔና ሰዋስው ወደሚያስተምር ወደሌላ መምህር ሄድኩ። (እዚያ) ከጓደኞቼ እያፈጠንኩ እንድማር እግዚአብሔር ጥበቡን ሰጠኝ። ይኽም በፊት ባሳዘነኝ ፈንታ አስደሰተኝ። እዚያ 4 ዓመት ቆየሁ።

በዚያን ዘመን እግዚአብሔር ከሞት አፍ ተፋኝ፤ ምክንያቱም ከጓደቼ ጋራ ስጫወት ገደል ገብቼ ነበር። እግዚአብሔር በተአምር እንደአዳነኝ እንጂ ሌላስ እንዴት እንደዳንኩ (B, 2r) አላውቅም። ከዳንኩ በኋላ ገደሉን በረጅም ገመድ ለካሁት፤ 25 ክንድ ከ1 ስንዝር ሆኖ ተገኘ። ምንም ሳልሆን ተነሥቼ ያዳነኝን እግዚአብሔርን እያመሰገንኩ ወደመምህሬ ቤት ሄድኩ[8]።

ከዚያ በኋላ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ ለመማር (ወደ መጽሐፍ ትምህርት ቤት) ሄድኩ። በዚህ ትምህርት 10 ዓመት አሳለፍኩ።[9] መጻሕፍቱን ፈረንጆች[10] እንደሚተረጒሟቸው፥ እንደገና ደግሞ ያገራችን መምህራን እንደሚተረጒሟቸው ተማርኩ። ግን ትርጓሜያቸው ብዙ ጊዜ ከኅሊናዬ ጋራ አይስማማም ነበረ። ሆኖም ዝም አልኩ፤ አስተያየቴን ሁሉ በልቤ ደበቅሁ።

ከዚያ በኋላ ወደ አክሱማዊት ሀገሬ ተመልሼ 4 ዓመት መጻሕፍት አስተማርኩ። ይህ ዘመን መጥፎ ዘመን ነበረ፤ ምክንያቱም በሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት በ19ነኛው ዓመት ከፈረንጆች ወገን አቡነ እፎንስ[11] (የሚባል ጳጳስ) መጥቶ ነበረ። (ከመጣ) ከ2 ዓመት በኋላ በሞላ

---

[8]መምህራን የሚያስተምሩት እቤታቸው ሆነው ስለሆነ "ወደ መምህሬ ቤት ሄድኩ" ማለት ወደ "ትምህርት ቤቴ ሄድኩ" ማለት ነው።
[9]የየትኞቹን መጻሕፍት ትርጓ እንደተማረ አይናገርም።
[10]ካቶሊኮች።
[11]Alfonso Mendez.

ኢትዮጵያ ከፍ ያለ ስደት ሆነ፤ (B, 2v) ምክንያቱም ንጉሡ የፈረንጆቹን ሃይማኖት ወዶ ነበረ። ስለዚህ ይኸንን ሃይማኖት ያልተቀበሉትን ሁሉ ያሳድዳቸው ጀመረ።

## ክፍል ሁለት

እኔም ሀገሬ ሆኜ መጻሕፍት ሳስተምር ከጓደኞቼ ብዙዎች ጠሉኝ፤ ምክንያቱም በዚህ ዘመን የጓደኛ ፍቅር ጠፍቶ ነበረ። ቅናትም ያዛቸው፤ ምክንያቱም በትምህርትና ጓደኛ በማፍቀር ከነሱ እበልጥ ነበረ። ከሰዎች ሁሉ ጋራም፥ ከፈረንጆቹም[12] ሆነ ከግብጻውያን[13] (ጋራም)፥ እስማማ ነበረ። ሳስተምርና መጻሕፍቱን ስተረጉም “ፈረንጆች እንዲህ፥ እንዲህ ይላሉ፤ ግብጻውያን እንዲህ፥ እንዲህ ይላሉ” እላለሁ፤ “እኛ ጥሩዎች ስንሆን ሁሉም ጥሩ ይሆናል” እላለሁ እንጂ “ይኸኛው ደኅና ነው፤ ይኸኛው መጥፎ ነው” አልልም። በዚህም ምክንያት ሁሉም ጠሉኝ፤ ምክንያቱም ለግብጻውያኑ ፈረንጅ ስመስላቸው ለፈረንጆቹ ግብጻዊ እመስላቸው ነበረ። (ሰዎች) ብዙ ጊዜ ከንጉሡ ዘንድ የውሸት ክስ አቀረቡብኝ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር አዳነኝ።

ከዚያ በኋላ ግን ከአክሱም ካህናት አንዱ ጠላቴ የሆነ ወልደ ዮሐንስ የሚሉት (ሊያጣላኝ) ወደንጉሡ ሄደ። የንጉሡ ወዳጅም ሆነ፤ መቸም (B, 3r) የንጉሦች ወዳጅነት የሚገኘው በሸንጋይ ምላስ ነው። ይህ ሸንጋይ ወደንጉሡ ሄዶ ስለኔ (እንዲህ) አለው፥ “በውነት ይህ ሰው ሰዎችን ያሳስታል፤ ለሃማኖታችን ልንነሣና ንጉሡን ልንገድለው፥ ፈረንጆችንም ልናሳድዳቸው ይገባል ይላቸዋል” (በሚልና) ይኸንንም በሚመስል ደጋግሞ ከሰሰኝ።

እኔም ይኸንን በጊዜው ዐውቄ ፈራሁ። ያለኝን ሦስት ወቄት ወርቅ፥ የምጸልይበትን መጽሐፍ፥ መጽሐፈ መዝሙረ ዳዊትን ይዤ በሌሊት ሸሸሁ። ወዴት እንደምሄድ ለማንም አልገለጥኩም። ወደ ተከዚ ወንዝ አቅጣጫ (ሄጄ) ከዱር ገባሁ። በማግሥቱ ረኀብ ያዘኝ። በፍርሃት ወጥቼ ከአገሩ ሀብታሞች [አንዱ] ዘንድ የሚበላ እንጀራ ልለምን ሄድኩ። ሰጡኝ፤ በልቼ በሽሽት ሄድኩ። ብዙ ጊዜ እንደዚሁ አደረግሁ።

---

[12]ከካቶሊኮቹም።
[13]ከተዋሕዶዎቹ።

ወደሸዋ ስሄድ ሰው የሌለ(በት) አንድ ዱር አገኘሁ። (እዚያ) ካንድ ትልቅ ገደል ስር ጥሩ ዋሻ አለ። "ሰዎች በማያውቁኝ ሁኔታ በዚህ እቀመጣለሁ" አልኩ። እስከ (አፄ) ሱስንዮስ ሞት ድረስም እዚያ 2 ዓመት ተቀመጥሁ። አንድ አንድ ጊዜ ወጣ (B, 3v) እልና ወደገበያ ወይም ከአምሐራ ሰፈሮች ወደአንዱ ብቅ እል ነበር። ለአምሐራ ሰዎች ምጽዋት የሚለምን ባሕታዊ መነኩሴ እየመሰልኳቸው የምበላውን ይሰጡኛል። የት እንደምኖር ግን ሰዎች አያውቁም።

በዋሻዬ ውስጥ ብቻዬን በነበርኩበት ጊዜ በመንግሥተ ሰማያት የምኖር መሰለኝ፤ ምክንያቱም፥ ቊጥር የሌለውን ክፋታቸውን ስለማውቅ ከሰው ጋራ መኖርን ጠልቼ ነበር። የዱር አራዊት ሌሊት እንዳይበሉኝ ዋሻዬን በሚከለክላቸው በድንጋይና በእሾህ አጥር አሳመርኳት። (ለክፋት) የሚፈልጉኝ ሰዎች ቢመጡብኝ እንዳመልጥ መውጫ አበጀሁ። እዚያ በሰላም ኖርኩ። በዳዊት መዝሙር በፍጹም ልቤ እየጸለይኩ በሚሰማኝ በእግዚአብሔር ተስፋ አደርግሁ።

## ክፍል ሶስት

ከጸሎት በኋላ ሥራ ስለሌለኝ ሁል ጊዜ ቊጭ ብዬ ስለሰው ጭቅጭቅ፥ ስለክፋታቸውም፥ ሰዎች በስሙ እያመፁ ጓደኞቻቸውን ሲያሳድዱ፥ ወንድሞቻቸውን ሲገድሉ ዝም ስለሚለው ስለፈጣሪያቸው ስለ እግዚአብሔር ጥበብ አስብ ጀመርኩ፤ (B, 4r) ምክንያቱም በዚህ ዘመን ፈረንጆቹ ኀይል አግኝተው ነበረ። ግን ፈረንጆቹ ብቻ ሳይሆኑ የአገር ሰዎችም ከነሱ የባሰ ከፍተዋል። የፈረንጆችን ሃይማኖት የተቀበሉት፥ "ግብጻውያን[14] እኮ ትክክለኛዋን የጴጥሮስ መንበርን ሃይማኖት ክደዋል፤ የእግዚአብሔር ፀሮች ናቸው" ይላሉ፤ በዚህም ያሳድዱቸዋል። ግብጻውያንም ስለራሳቸው ሃይማኖት እንደዚሁ ያደርጋሉ።

አስቤ (እንዲህ) አልኩ፡- "የሰዎች ጠባቂያቸው እግዚአብሔር ከሆነ ተፈጥሯቸው እንዴት እንደዚህ ተበላሸ?" (እንዲህ) አልኩም፡- "እግዚአብሔር እንዴት ያውቃል? እንዲያውስ በሰማይ ሆኖ የሚያውቅ (አምላክ) አለ ወይ?"[15] የሚያውቅ (አምላክ) ካለ ስለሰዎች ክፋት፥ ስሙን ሲያረኩሱት፥ በቅዱስ ስሙም ዓመፅ ሲሠሩ፥ እንዴት ዝም ይላል?"

---

[14]ኦርቶዶክሶች።
[15]መዝ. 72፥11.

(በዚህ ነገር) ብዙ አሰብኩ፤ ግን አልታይህ አለኝ። (እንዲህ) ብዬም ጸለይኩ፡- "ጌታዬ፥ ፈጣሪዬ፥ አስተዋይ አድርገህ የፈጠርከኝ ሆይ፤ አሳየኝ፥ ስውር ጥበብህንም ግለጽልኝ። ዓይኖቼ ለሞት እንዳይተኙ አብራቸው።"[16] እጆችህ ሠርተውኛል፤ ቀርጸውኛልም። ትእዛዝህን እማር ዘንድም ልቡና ስጠኝ።"[17] (B, 4v) እኔ ግን እግሮቼ ፈጽሞ እንዲሁ የሚንገዳገዱ ናቸው፤ ሰኮናዎቼንም እንዲሁ የሚያድጣቸው ናቸው።[18] ይህስ በፊቴ ድካም ነው።" ይኽንንና የመሰሉትን ስጸልይ ቆየሁ።

ከዕለታት አንድ ቀን አስቤ (አስቤ እንዲህ) አልኩ፡- "ወደማን ዘንድ ነው የምጸልየው? (ለመሆኑ) የሚሰማኝ እግዚአብሔር አለ ወይ?" በዚህ ሐሳብ በጣም ተከዝኩ። ዳዊት እንዳለውም (እንዲህ) አልኩ፡- "በውኑ ልቤን በከንቱ አጸድቃታለሁን?"[19] ከዚያ በኋላም ይኸው ዳዊት "ጆሮዎችን የተከላቸው አይሰማምን?"[20] ያለውን አሰብኩ። "በውኑ እንድሰማ ጆሮ የሰጠኝ ማነው? አስተዋይ አድርጎስ የፈጠረኝ ማነው? እንዴትስ እኔ ወደዚህ ዓለም መጣሁ? ከየትስ መጣሁ? የሕይወቴን ጥንትና[21] የዕውቀቴን ጥንት[22] ለማወቅ ከዓለም በፊት አልነበርኩም። ታዲያ ማን ፈጠረኝ? እኔው ራሴ በራሴ ተፈጠርኩን?" (እንዲህ እንዳልል) ደግሞ የተፈጠርኩ ጊዜ አልነበርኩም። "አባቴና እናቴ ፈጠሩኝ" ብል ደግሞ፥ እንደኛ ካልተወለዱት፥ ወላጅ ሳይኖራቸው ወደዚህ ዓለም በሌላ መንገድ ከመጡት (B, 5r) ከጥንታውያን እስኪደረስ ድረስ ለወላጆቼና ለወላጆቻቸውም ፈጣሪ ሊፈለግላቸው ነው። እነሱም የተወለዱ ከሆነ የትውልዳቸው ጥንት[23] ከየት ነው? "ከሌለ ነገር የፈጠራቸው፥ እሱ ግን ያልተፈጠረ፥ ያለና ለዘላለም የሚኖር[24]፥ የሁሉ ጌታ፥ ሁሉን የያዘ፥ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው፥ የማይለወጥና ዓመቶቹ የማይቈጠሩ አንድ ነባር አለ" ከማለት በቀር ሌላ አላውቅም። "ፈጣሪስ በውኑ አለ" አልኩ፤ ምክንያቱም ፈጣሪ ከሌለ ፍጥረት ባልተገኘም

---

[16] መዝ. 12፥4.
[17] መዝ. 118፥73.
[18] መዝ. 73፥2.
[19] መዝ. 72፥ 13.
[20] መዝ. 93፥9.
[21] "Origin."
[22] "Origin."
[23] "Origin."
[24] ራእይ ምዕ. 1፥4.

ነበረ። እኛ ስላለንና ፍጡሮች እንጂ ፈጣሪዎች ስላይደለንም፥ “የፈጠረን ፈጣሪ አለ” ማለት አለብን።

ይኸ፥ አስተዋዮችና አሳቢዎች[25] አድርጎ የፈጠረን ፈጣሪ የማያስተውልና የማያስብ[26] አይሆንም፤ ምክንያቱም አስተዋዮች አድርጎ የፈጠረን ከአስተዋይነቱ በተትረፈረፈው (አስተዋይነቱ) ነው። እሱስ ሁሉንም ስለፈጠረና ሁሉንም ስለያዘ ሁሉንም የሚያስተውል ነው። “ፈጣሪዬ ወደ እሱ ስጸልይ ይሰማኛል” አልኩና በዚህ ሐሳብ ታላቅ ደስታ ተደሰትሁ። በታላቅ ተስፋም ጸለይኩ፤ ፈጣሪዬንም በሞላ ልቤ አፈቀርኩት። (እንዲህም) አልኩ፦ “ጌታ ሆይ፥ አንተ የልቤን ሐሳብ ሁሉ ከሩቁ ታውቃለህ፤”[27] (B, 5v) እነሆ አንተ የቀድሞውንም የወደፊቱንም ሁሉ ዐውቀሃልና። መንገዴን ሁሉ አንተ አስቀድመህ ዐውቀሃል።”[28] ስለዚህ (ዳዊት) “ከሩቅ ታውቃለህ” አለ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር እኔ ከመፈጠሬ በፊት ሐሳቤን ዐውቋልና። እኔም፥ “የኔ ፈጣሪ ሆይ፥ ልብ እንድል አስችለኝ” አልኩ።

## ክፍል አራት

ሳስብ ከቆየሁ በኋላ (እንዲህ) አልኩም፤ “በቅዱሳቱ መጻሕፍት ውስጥ የተጻፈው ሁሉ እውነት ነውን? ብዙ አሰብኩ፤ ግን ፈጽሞ አልተረዳሁም። “ምሁራንንና ተመራማሪዎችን ሄጄ ልጠይቅ፤ እውነቱን ይነግሩኛል” አልኩ። ከዚህ በኋላ አሰቤ (እንዲህ) አልኩ፤ “ሰዎች (ብጠይቃቸው) በልባቸው ካለው በተቀር (ሌላ) ምን ይመልሱልኛል? ምክንያቱም፥ ሰው ሁሉ “ሃይማኖቴ ትክክለኛ ነች፤ በሌላ ሃይማኖት የሚያምኑ በውሸት ያምናሉ፤ የእግዚአብሔር ጠላቶች ናቸው” ይላሉ። ዛሬም እኮ ፈረንጆች፥ “የኛ ሃይማኖት ጥሩ ናት፤ የናንተ ሃይማኖት መጥፎ ናት” ይሉናል። እኛም ደግሞ፥ “እንደዚህ (እንደምትሉት) አይደለም፤ የናንተ ሃይማኖት መጥፎ ናት፤ የኛ ሃየማኖት ልክ ናት” ብለን እንመልስላቸዋለን። እንዲሁም እስላሞችንና (B, 6r) አይሁዶችን ብንጠይቃቸው እነሱም እንደዚሁ ባሉን። በዚህ ክርክር ማን ፍርድ ሰጪ ይሆናል? ከሰው ማህል አንዱም (ፍርድ ሰጪ) አይሆን፤ ምክንያቱም ሰዎች ሁሉ እርስ በርሳቸው ከሳሽና ተከሳሽ ናቸው።

---

[25]“Rational.”
[26]“ Irrational.”
[27]መዝ. 138፥2.
[28]መዝ. 138፥3.

መጀመሪያ አንዱን የፈረንጅ መምህር ስለ የሃይማኖታችን ነገር ብዛት[29] ጠየኩት። እሱም ስለሁሉም ከራሱ ሃይማኖት አንጻር ፍርዱን ሰጠ። ከዚህ በኋላ አንዱን ትልቅ ኢትዮጵያዊ መምህር ጠየቅሁት። እሱም ስለሁሉም ከራሱ ሃይማኖት አንጻር ፍርዱን ሰጠ። እስላሞችንና አይሁዶችንም ብንጠይቅ እነሱም እንደዚሁ ከሃይማኖታቸው አንጻር ነው የሚፈርዱት። እውነትን የሚፈርድ ከየት አገኛለሁ? ምክንያቱም እውነቱ ለኔ እንደ ሃይማኖቴ እንደሚመስለኝ ለሌላውም እንደዚሁ እውነቱ እንደ ሃይማኖቱ ይመስለዋል። እውነት ግን አንድ ናት።

እንዲህ እያሰብኩ (እንዲህ) አልኩ፡- "አስተዋይ አድርገህ የፈጠርከኝ፥ የጥበበኞች ጥበበኛ፥ የእውነተኞች እውነተኛ የሆንክ ፈጣሪዬ ሆይ፥ አንተ ግለጽልኝ፤ ምክንያቱም ዳዊት፥ "ሰው ሁሉ ውሸተኛ ነው"[30] ከሚለው በቀር ከሰው ዘንድ ጥበብም ሆነ እውነት አይገኝም።

አስቤም (እንዲህ) አልኩ፤ (B, 6v) "በዚህ በትልቅ ጉዳይ ሰዎች ራሳቸውን ለማጥፋት ለምን ይዋሻሉ?" የሚዋሹት ምንም ስለማያውቁ የሚያውቁ እየመሰላቸው መሰለኝ። በዚህም ምክንያት እውነትን ለማግኘት አይመራመሩም። ዳዊት፥ "ልባቸው እንደወተት ረግቷል"[31] ይላል። እነሱም ከቀደሚቸው (ሰዎች) በሰሙት ልባቸው ረግቶ እውነት ይሁን ሐሰት አልተመራመሩም። እኔም "አገዛዝህን አውቅ ዘንድ ያሳመምከኝ በሚገባኝ ነው። አንተ በእውነት ገሥጸኝ፤ በምሕረትም ንቀፈኝ። የኀጢአተኞችንና የሐሰተኞችን መምህሮች ቅባት ግን ራሴን አልቀባም።'[32] አስተዋይ አድርገህ ፈጥረኸኛልና ግለጽልኝ" አልኩ።

አስቤም (እንዲህ) አልኩ፤ "አስተዋይ ከሆንኩ ምንድነው የማስተውለው?" (እንዲህም) አልኩ፡- "ከፍጥረት ሁሉ የሚበልጥ ፈጣሪ እንዳለ ይታየኛል። ምክንያቱም ከተትረፈረፈው ትልቅነቱ ትልቆችን ፈጥሯልና፤ ሁሉን የሚያስተውል አስተዋይም ነው፤ ምክንያቱም ከተትረፈረፈው አስተዋይነቱ አስተዋዮች አድርጎ ፈጥሮናልና። ልንሰግድለትም ይገባናል፤ ምክንያቱም የሁሉ ጌታ ነውና።[33] ሁሉን የያዘ ስለሆነ ወደእሱ ስንጸልይ ይሰማናል።"

---

[29]"ስለ ብዙ የሃይማኖት ነገር" ለማለት ፈልጎ ይመስላል።
[30]መዝ. 115፥2.
[31]መዝ. 118፥70.
[32]መዝ. 140፥5.
[33]ሁሉንም የደረሰበት አስቦ ከሆነ፥ ለጌታ እንደሚሰገድ እንዴት ቢያስብ ደረሰበት?

አስቤም (እንዲህ) አልኩ፤ (B, 7r) "እግዚአብሔር አስተዋይ አድርጎ ከፈጠረኝ እንዲሁ ለከንቱ ለእንደዚሁ አልፈጠረኝም፤ ተመራምሬ እሱንና ጥበቡን በፈጠረኝ መንገድ እንዳስተውለውና እስካለሁ ድረስ እንዳመሰግነው ነው እንጂ።"

አስቤም (እንዲህ) አልኩ፤ "ሰዎች ሁሉ ሐሰትን እንጂ እውነትን የማያስተውሉት ለምንድነው?" (ምክንያቱ) የሰው ተፈጥሮው ደካማና ስልቹ ስለሆነ መሰለኝ። ሰው እውነትን ይወዳል፤ አጥብቆም ያፈቅራታል። የተፈጥሮን ስውር ነገሮች ማወቅ ይፈልጋል። ግን ነገሩ አስቸጋሪ ነው፤ ያለ ትልቅ ጥረትና ትዕግሥት አይገኝም፤ ሰሎሞን እንዳለው፥ "ከፀሐይ በታች ስለተፈጠረው ሁሉ ልቤን ለምርመራና በጥበብ ለመፈተን ሰጠሁ፤ ምክንያቱም ይደክሙበት ዘንድ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ክፉ ድካምን ሰጥቷቸዋል።"[34] ስለዚህ ሰዎች መመራመርን አይፈልጉም፤ ከአባቶቻቸው የሰሙትን ያለ ምርምር ማመንን ይመርጣሉ እንጂ።

አንድ ሰው ደግም ሆነ ወይም መጥፎ እንደፈለገ እንዲሆን እግዚአብሔር የሥራው ባለቤት አድርጎ ፈጥሮታል። አንድ ሰው (B, 7v) ክፉና ውሸታም ለመሆን ከመረጠ ለክፋቱ የሚገባውን ቅጣት እስኪያገኝ ድረስ (ያንን ለመሆን) ይቻለዋል። ደግሞ ሰው ሥጋዊ ነውና ለሥጋው የሚሻለውን ይወዳል። ለሥጋው የሚያስፈልጉትን በደግም ሆነ በክፉ ባገኘው መንገድ ሁሉ ይፈልጋል። እግዚአብሔር ሰውን የፈለገውን ለመሆን ምርጫን ሰጥቶ እንጂ ክፉ አድርጎ አልፈጠረውም። በዚህም ምርጫ ደጎና ከሆነ ለዋጋ፥ መጥፎ ከሆነ ለቅጣት የተዘጋጀ ይሁን፥ ገንዘብ (ማግኘትን) ወይም በሰው ዘንድ መከበርን የሚፈልግ ውሸተኛ ሰው ይኽንን በውሸት መንገድ የሚያገኘው ከሆነ ውሸትን እውነት እያስመሰለ ይናገራል። (የሚናገረው) ምርምርን ለማይፈልጉ ሰዎችም እውነት ይመስላቸዋል። ጽኑ በሆነ እምነትም ያምኑበታል።

እስቲ ሕዝባችን በስንት ውሸት (ነገር) ያምናል? በኮከብ ቈጠራና በሌሎችም (የጥንቈላ) ሐሳቦች ጽኑ በሆነ እምነት ያምናሉ። በድብቅ አስማት፥ በፋል፥ ጋኔን በመሳብ፥ በመርጨት[35] እና በጠንቋዮች ጣጣ ሁሉ (ያምናሉ)። (B, 8r) በዚህ ሁሉ የሚያምኑት መርምረው እውነትን ስላገኟት አይደለም፤ ቀድመዋቸው ከነበሩ ስለሰሙት ያምናሉ እንጂ። እነዚያ ቀድመዋቸው የነበሩትም ገንዘብ ወይም ክብር ለማግኘት

---

[34] መክ 1፥13.
[35] "Exorcism."

ሲሉ ካልሆነ ለምን ዋሹ? እንደዚሁም በሰዎች ላይ ሥልጣን እንዲኖራቸው የሚፈልጉ (ሰዎች)፥ "እውነትን እንድንነግራችሁ እግዚአብሔር ወደናንተ ልኮናል" አሉ። ሰዎችም አመኑ። ከነሱ በኋላ የመጡም አባቶቻቸው ያለምርምር የተቀበሉትን እምነት አልተመራመሩም። እንዲያውም የሃይማኖታቸውን እውነተኛነት ለማስረዳት የምልክቶችና የታምሮች ታሪክ እየጨመሩበት አጸኑት። "እግዚአብሔር ይኸንን ሠራ" እያሉ እግዚአብሔርን የሐሰት ምስክርና የዋሾች ግብር አበር አደረጉት።

## ክፍል አምስት

ለተመራማሪ ግን እውነት ፈጥና ትገለጣለች፤ ምክንያቱም ፈጣሪ በሰው ልብ ውስጥ ባስቀመጠው ንጹሕ ልቦና የሚመረምር (ሁሉ) የተፈጥሮን ሥርዐትና ሕጎች አይቶ እውነትን ያገኛል።

(ለምሳሌ) ሙሴ "ፈቃዱንና ሕጉን እንድነግራችሁ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላክሁ"[36] አለ። ከሱ በኋላ የመጡቱ (ሰዎች) (B, 8v) "በምድረ ግብጽና በደብረ ሲና የተሠሩ ናቸው" ብለው የታምራት ታሪክ ጨመሩበትና የሙሴን ነገር እውነት አስመሰሉት። ለተመራማሪ ግን (ይህ ሁሉ) እውነት አይመስለውም፤ ምክንያቱም በሙሴ መጻሕፍት ውስጥ ከፈጣሪ ጥበብም ሆነ ወይም ከተፈጥሮ ሥርዐትና ሕጎች ጋራ የማይስማሙ መጥፎ ጥበብ ይገኛል። ምክንያቱም የሰው ፍጥረት እንዳይጠፋ ልጆች ለመውለድ በፈጣሪ ፈቃድና በተፈጥሮ ሥርዐት ወንድና ሴት በሥጋዊ ግንኙነት ይገናኙ ዘንድ ታዟል።[37] እግዚአብሔር በሰው የተፈጥሮ ሕግ ውስጥ ያቆመው ይኸ (የሥጋ) ግንኙነት[38] እርኵኵስ ሊሆን አይችልም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር የጁን ሥራ አያረኩስም። ሙሴ ግን "(የሥጋ) ግንኙነት ሁሉ እርኩስ ነው"[39] አለ። ግን ይኸንን የሚል ውሸተኛ እንደሆነና ይኸንን የፈጠረውንም ውሸተኛ እንዳደረገው ልቦናችን ይነግረናል።

---

[36]ዘፀ 3፡113.

[37]በግምት ደርሶበት እንጂ ሙሴን ሐሰተኛ ነቢይ ካደረገው በኋላ "ብዙ ተባዙ" ያለውን የሙሴን ቃል (ዘፍ 1፡18) መጥቀሱ አይደለም።

[38]ወሲብ።

[39]እንዲህ ያለ ጥቅስ ከሙሴ መጻሕፍት አይገኝም። የሚለው ከዘመዶቻችሁ ጋር የወሲብ ግንኙነት አታድርጉ ነው፤ ሌዋ 18.

ዳግመኛም፥ "የክርስቲያን ሕግ ከእግዚአብሔር ዘንድ (የተገኘች) ናት" አሉ። ለማስረጃዋ (የሚሆኑ) ታምራትም ተገኝተዋል። ግን ጋብቻ[40] ፈጣሪ (ካቆማቸው) ሥርዐቶች ውስጥ እንደሆነ ልቡናችን ይነግረናል፤ ያስረዳናልም። (B, 9r) ምንኵስና ታዲያ የፈጣሪን ጥበብ ይሽራል፤ ምክንያቱም ልጆች መውለድን ይከለክላል፤ የሰውንም ፍጥረት ያጠፋል። የክርስቲያን ሕግ "ምንኵስና ከጋብቻ ይሻላል" ስትል ውሸት ተናግራለች።[41] ከእግዚአብሔር አይደለችም፤ ምክንያቱም የፈጣሪን ሕግ የሚያፈርስ (ሥርዐት) እንዴት ከእሱ ጥበብ ይሻላል? የሰው ሐሳብ የእግዚአብሔርን ሥራ ሊያሻሽለው ይችላልን?

እንደዚሁ፥ መሐመድም "የማዛችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበልኩትን ነው" አለ። የመሐመድን (ከእግዚአብሔር) መልላክ የሚያስረዱ ታምራት ጸሐፊዎችም አልታጡም፤ አመኑበትም። እኛ ግን የመሐመድ ትምህርት ከእግዚአብሔር ዘንድ ሊሆን እንዳማይችል እናውቃለን፤ ምክንያቱም የሚወለደው ሰው ወንዱና ሴቱ በቍጥር እኩል ናቸው። በአንድ የተወሰነ አገር ያሉትን ወንዶችና ሴቶች ብንቆጥራቸው አንዲት ሴት ለየአንዳንዱ ወንድ ትደርሳለች፤ ስምንት ወይም ዓሥር ሴት ለየአንዳንዱ ወንድ አይደርስም፤ ምክንያቱም አንዱ ከአንዲቷ ጋራ ይጋቡ ዘንድ የተፈጥሮ ሕግ ታዛለች። አንድ ወንድ ዓሥር ሴት ካገባ ሚስት የሌላቸው ዘጠኝ ሰዎች ይተርፋሉ። ይኸም የፈጣሪን ሥርዐትና የተፈጥሮን ሕጎች ያፈርሳል። የጋብቻንም ጥቅም ዋጋ ቢስ ያደርገዋል። (B, 9v) አንድ ወንድ ብዙ ሴቶች ማግባት ይገባዋል ብሎ በእግዚአብሔር ስም ያስተማረ መሐመድ ውሸተኛ ነው፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ አልተላከም።

ስለጋብቻ ሕግ ይኸንን በጥቂቱ መረመርኩ። እንደዚሁ በኦሪት ሕግ፥ በክርስቲያን ሕግ፥ በእስላም ሕግ ውስጥ የቀረውን (ሁሉ) ስመራመር ልቡናችን ከሚገልጽልን እውነትና ከፈጣሪያችን ቀጥታ ጋራ የማይስማማ ብዙ (ነገር) አገኘሁ፤ ምክንያቱም ፈጣሪ በሰው ልብ ውስጥ ደግና ክፉ እንዲያይ፥ የሚገባውንና የማይገባውን እንዲያውቅ፥ እውነትን ከውሸት እንዲለይ የልቡና ብርሃን አስቀምጧል። "ጌታ ሆይ፥ በብርሃንህ ብርሃን እናይ ዘንድ"[42] (እንዳለ)። ይህ የልቡናችን ብርሃን እንደሚገባ ብናይበት ሊደልለን አይችልም፤ ምክንያቱም

---

[40] ወሲብ።
[41] ካቶሊኮቹ ይሉ እንደሆን እንጂ ኦርቶዶክሶች አይሉም።
[42] መዝ 35፥10.

ፈጣሪያችን ይኸንን ብርሃን የሰጠን እንድንድንበት እንጂ እንድንጠፋ አይደለም። የልቡናችን ብርሃን የሚያሳየን ሁሉ ከእውነት ምንጭ (የሆነውን) ነው።

ሰዎች የሚነግሩን ግን ከውሸት ምንጭ ነው። ፈጣሪ ያቆመው ሥርዐት ሁሉ ትክክል እንደሆነ ልቡናችን ያስረዳናል። (ለምሳሌ) ፈጣሪ በጥሩ ጥበብ ከሴት ማሕፀን በየወሩ ደም እንዲፈስ ሥርዐት አቁሟል። (B, 10r) ይህ የደም መውረድ ለሴት ሕይወትና ልጆች ለመውለድ ያስፈልጋል። ይህ የማይወርዳት ሴት መካን ነች፤ መውለድ አትችልም። ምክንያቱም ፍጥረቷ ተበላሽቷል። ሙሴና ክርስቲያኖች ግን ይኸንን የፈጣሪ ጥበብ እርኩስ አደረጉት። ሙሴማ እንዲያውም በእንዲህ ያለች ሴት የተነካውንም ሁሉ ርኩስ ያደርጋል።[43] ይኸ የሙሴ ሕግ ጋብቻንና የሴትን ሕይወት ከባድ ያደርጋል፤ የመረዳዳትንም ሕግ ይሽራል፤ ልጆች ማሳደግን ይነሣል፤ ፍቅርንም ያስቀራል። ስለዚህ ይኸ የሙሴ ሕግ ሴትን ከፈጠረ (አምላክ የመጣ) ሊሆን አይችልም።

ደግሞ ልቡናችን፥ የሞቱ ወንድሞቻችንን እንቀብራቸው ዘንድ የሚገባ ይሁን ይለናል። በድኖቻቸውም በሙሴ ጥበብ እንጂ ወደመሬት እንመለስ ዘንድ ከመሬት በፈጠረን[44] ፈጣሪያችን ዘንድ እርኩሶች አይደሉም።[45] ለማንኛውም እግዚአብሔር ለሰው ተፈጥሮ ሁሉ እንደሚገባው (አድርጎ) በታላቅ ጥበብ ያቆመውን የራሱን ሥርዐት (መልሶ) አያረኩስም። ሰው ግን የውሸት ቃልን ለማክበር ሲል ሊያረኩሰው ይፈልጋል።

ደግሞ ወንጌል፥ "አባቱንና እናቱን፥ ሚስቱንና ልጆቹን ያልጣለ (B, 10v) ለእግዚአብሔር የተገባ አይደለም" ትላለች።[46] ይህ አጣጣል የሰውን ፍጥረት ሁሉ ያበላሻል፤ እግዚአብሔር ፍጥረቱን በማበላሸት አይደሰትም። አባትና እናት ባረጁ ጊዜ ረዳት በማጣት (ምክንያት) እንዲሞቱ መጣል ትልቅ ኀጢአት እንደሆነ ልቡናችን ያሳየናል። እግዚአብሔር እኮ ዐመፃ የሚወድ አምላክ አይደለም። ልጅን መጣል ግልገሎቻቸውን ከማይጥሉ ከዱር አራዊት የከፋ (ያደርጋል)። ሚስቱን የሚጥል ደግሞ እንድታመነዝር ያደርጋታል። (ይህ) ሁሉ የፈጣሪን

[43]ሌዋ 15፡19.
[44]የሙሴን ነቢይነት ካላመነ፥ ከመሬት መፈጠራችንን በምን ዐወቀው? በምርምር ሊደርስበት አይችልም።
[45]ሌዋ 21፡11.
[46]ማቴ 10፡37. ሉቃ 14፡26.

ሥርዐትና የተፈጥሮን ሕግ ያፈርሳል። ስለዚህ ወንጌል በዚህ ክፍል የተናገረችው ከእግዚአብሔር (የመጣ) ሊሆን አይችልም።

ደግሞም እስላሞች፥ "ሰውን እንደ እንስሳ መሸጥና መግዛት ይገባል" ይላሉ። ነገር ግን ይኽ የእስላም ሕግ ፈጣሪያችንን አባታችን እንድንለው እንደወንድማማቾች እኩል አድርጎ ከፈጠረን ከሰው ፈጣሪ ዘንድ ሊወጣ አይችልም። መሐመድ ግን ደካማውን ሰው የኀይለኛ ሰው ንብረት አደረገው። (በዚህም) አስተዋዩን ፍጥረት አስተዋይ ካልሆነ እንስሳ ጋራ እኩል አደረገው። ይኽ (B, 11r) አመፃ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሊወጣ ይችላልን?

እንደዚሁም እግዚአብሔር ከንቱ ነገር አያዝም፤ (እንዲህም) አይልም፤ "ይኽንን ብላ፤ ይኽንን (ግን) አትብላ።"[47] የቤተ ክርስቲያንን የጾም ሕጎች የሚጠብቁ (ሰዎች) እንደሚመስላቸውም፥ "ዛሬ ብላ፥ ነገ አትብላ፤ ዛሬ ሥጋ አትብላ፥ ነገ ግን ብላ" አይልም።[48] እስላሞችንም እግዚአብሔር "ሌሊት ብሉ፥ ቀን ግን አትብሉ"[49] እና ይኽንን የሚመስለውን አላላቸውም፤ ምክንያቱም ጤናችንንና ተፈጥሯችንን የማያበላሸውን ሁሉና በየቀኑም ሕይወታችንን (ለማቆየት) የሚበቃንን ያህል እንበላ ዘንድ እንደተፈቀደልን ልቡናችን ያስተምረናል። አንድ ቀን መብላት፥ አንድ ቀን መጾም ጤና ያበላሻል፤ የመጾም ሕግ ለሰው ሕይወት መብሎችን ከፈጠረና በልተናቸው እንድናመሰግነው ከፈቀደ ፈጣሪ ሥርዐት ውጪ ነው። ከበረከቱ እንከለከል ዘንድ አይገባንም።

"የጾም ሕግ የተሠራው የሥጋን ፍትወት ለመግደል ነው" የሚሉኝ ካሉ (እንዲህ) እላቸዋለሁ፤ "በሰው ላይ ያለ የሥጋ ፍትወት ወንድ ወደሴት የሚሳብበት፥ ሴትም ወደወንድ የምትሳብበት (B, 11v) የፈጣሪ ጥበብ ነው። ይኽንን በታወቀው፥ እሱ ፈጣሪ በአቆመው ሥርዐት፥ በሥጋዊ መገናኘት ካልሆነ በቀር (በሌላ መንገድ) ማብረድ አይገባም፤ ምክንያቱም ፈጣሪያችን ይኽንን ፍትወት በሰውና በእንሳሰት ሥጋ ሁሉ በከንቱ አላስቀመጠውም። ይኽንን ፍትወት በሰው ሥጋ ላይ የተከለው ለዚች ዓለም የሕይወቱ መሠረት እንዲሆንና ፍጥረትን ሁሉ በአቆመለት ሥርዐት መንገድ እንዲያጸናው ነው።

[47] ሌዋ 11.
[48] ሲኖዶስ፡
[49] ቁርአን 2፡187.

ይህ ፍትወት ከወሰን እንዳያልፍ የሚያስፈልገንን ያህል (ብቻ) እንብላ፤ ምክንያቱም ጥጋብና ስካር ጤንነትንና ምግባርን ያበላሻል። ግን እሑድ እሑድና በበዓለ ኃምሳ (ጦም በሌለበት ጊዜ) የሚያስፈልገውን ያህል የሚበላ ኀጢአት እንደማይሆንበት፥ እንዲዚሁም በዓርብ ቀንና ከፋሲካ በፊት ባሉት ቀናት የሚበላም ኀጢአት አይሆንበትም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ሰውን በየቀኑና በየወሩ ሁሉ እኩል ከመብላት ፍላጎት ጋራ ነው የፈጠረው። አይሁድም፥ ክርስቲያኖችም፥ እስላሞችም የጾምን ሕጎች ሲያወጡ (B, 12r) ይኸንን የእግዚአብሔርን ሥራ ልብ አላሉትም። “እግዚአብሔር ጾምን በሥርዐት አቁሞልናል፤ መብላትንም ከልክሎናል” ሲሉ ይዋሻሉ፤ ምክንያቱም ፈጣሪያችን እግዚአብሔር የምግባችንን መብሎች የሰጠን እንድንመገባቸው እንጂ፥ ከነሱ እንድንከለከል አይደለም።

## ክፍል ስድስት

ሌላም ትልቅ ምርምር አለ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ሰዎች ሁሉ እኩል ናቸው፤ አስተዋዮች ሁሉ የሱ ፍጥረቶች ናቸው። እሱ አንዱን ሕዝብ ለሕይወት፥ አንዱን ለሞት፥ አንዱን ለምሕረት፥ አንዱን ለኵነኔ አልፈጠረውም። በሥራው ሁሉ እውነተኛ በሆነው በእግዚአብሔር ዘንድ ይኸ አድልዎ እንደማይገኝ ልቡናችን ያስተምራናል።

ታዲያ ሙሴ አይሁድን ብቻ ሊያስተምር ተላከ። ራሱ ዳዊትም፥ “ለሎች ሕዝቦች እንደነሱ (ለአይሁድ እንዳደረገው) አላደረገም፤ ፍርዱንም አልነገራቸውም”[50] ይላል። እግዚአብሔር ፍርዱን ለአንድ ሕዝብ ነግሮ ለሌላው ያልነገረው ለምንድን ነው?

በዚህ (ባለንበት) ዘመን ክርስቲያኖቹ፥ “የእግዚአብሔር ትምህርት ከኛ ዘንድ በቀር አይገኝም” ይሉናል። አይሁድም፥ እስላሞችም፥ ህንዶችም፥ ሌሎችም እንደዚሁ ይላሉ። ደግሞ (B, 12v) ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው አይስማሙም። ፈረንጆቹ፥ “የእግዚአብሔር ትምህርት ያለው እኛ ዘንድ እንጂ እናንተ ዘንድ የለም” ይሉናል። እኛም (ስለራሳችን) እንደዚሁ ነው የምንለው። ሰዎችን ስንሰማቸው (እንደምንሰማቸው ከሆነ) የእግዚአብሔር ትምህርት በጣም ጥቂት ከሆኑት ዘንድ ካልሆነ በተቀር ከማንም ዘንድ አልደረሰም። ደግሞ

---

[50] መዝ 147፥20.

ከነዚህ ሁሉ ከማን ዘንድ እንደደረሰ አናውቅም። እግዚአብሔር ከፈለገ ቃሉን በሰዎች (ሁሉ) ዘንድ ማጽናት አቅቶት ነውን? ግን የእግዚአብሔር ጥበብ (ሆኖ)፥ በጥሩ ሐሳብ፥ ሰዎች እውነት መስሏቸው በውሸት ነገር ላይ እንዲስማሙ አልተዋቸውም፤ ምክንያቱም ሰው ሁሉ በአንድ ነገር ቢስማማ ነገሩ እውነት ይመስል ነበረ። ሰዎች ሁሉ በሃይማኖታቸው በምንም እንደማይስማሙ በሐሰት ነገር አይስማሙም።

እስቲ እናስብ፤ ለምንድነው? ይኸ የምናየው ሁሉ የተፈጠረ እንደሆነ፥ (B, 13r) ፍጡር ያለ ፈጣሪ እንደማይገኝ፥ ፈጣሪ እንዳለ እውነት መሆኑን የሰው ሁሉ ልቡና ያውቃል። በዚህ ሰዎች ሁሉ ይስማሙበታል። ሰዎች ያስተማሯቸውን ሃይማኖቶች ስንመረምራቸው ግን በውስጣቸው በእውነት ላይ ውሸት ተጨምሮ (እናገኛለን)። ስለዚህ አንስማማባቸውም፤ ሰዎች እርስ በርሳቸው ይነታረኩ(ባቸዋል)። እንዱ፥ "እንዲህና እንዲህ እውነት ነው" ሲል፥ ሌላው፥ "የለም፥ (እሱማ) ውሸት ነው" ይላል። የሰውን ቃል የእግዚአብሔር ቃል እያደረጉ ሁሉም ይዋሻሉ።

አሰብኩና (እንዲህ) አልኩ፤ "የሰው ሃይማኖት ከእግዚአብሔር ባትሆንም ቅሉ በሰዎች ዘንድ ትፈለጋለች፤ ደግ ሥራ (እንዲሠሩ) ታስገድድላቸዋለች፤ ማለት፥ ክፉዎች ክፉ ሥራ እንዳይሠሩ ታስፈራራቸዋለች፤ ደጎችን ደግሞ በትዕግሥታቸው ታበረታታቸዋለች። ለእኔ እንደዚህ ያለችው ሃይማኖት፥ ባሏ ሳያውቅ በዝሙት እንደወለደች ሚስት ትመሰላለች። ባሏ ልጁ በመሰለው ሕፃን ይደሰታል፤ (እናቲቱንም) ያፈቅራታል። (B, 13v) ከዝሙት እንደወለደችው ቢያውቅ ያዝናል፤ ሚስቱንም ከነልጇ ያባርራታል። እንደዚሁም እኔ ሃየማኖቴ ዘማ ወይም ውሸተኛ መሆኗን ካወቅሁ በኋላ ስለሷና በዝሙቷ (ስለወለደቻቸው) ልጆቿ አዘንኩ። (ልጆቿ የምለው) ወደ እዚህ ዋሻ የሰደዱኝን ጥልን፥ ስደትን፥ ዱላን፥ እስራትን፥ ሞትን ነው። ሆኖም እውነቱን ለመናገር፥ ይህቺ የክርስቲያኖች ሃይማኖት በወንጌል ዘመን ጊዜ እንደተደነገገችው (ቢሆን) ክፉ አይደለችም፤ ምክንያቱም ሰዎችን በእርስ በርስ ፍቅር (እንዲኖሩ) እና የምሕረትን ሥራ ሁሉ (እንዲሠሩ) ታዛቸዋለች። በዚህ ዘመን ግን ያገራችን ሰዎች የወንጌልን ፍቅር ወደጥል፥ ወደጨቋኝነት፥ ወደእባብ መርዝ አዞሩት። ሃይማኖታቸውን ከመሠረቷ ንደው ከንቱ (ነገር) ያስተምራሉ፤ አመፃ እየሠሩ በውሸት ክርስቲያን ይባላሉ።

## ክፍል ሰባት

አስቤም (እንዲህ) አልኩ፤ እግዚአብሔር ውሸተኛ ሰዎች ሕዝቦቹን እንዲያሳስቱ ለምንድነው የሚተዋቸው? ግን (እንዲህ ነው፤) እግዚአብሔር ሁሉም እውነትንና ውሸትን እንዲያውቅ ለያንዳንዳቸው ልቡና ሰጥቷቸዋል። እውነትን ወይም ውሸትን እንደፈለጉ የሚመርጡበትን የምርጫን ጸጋ ሰጥቷቸዋል። (B, 14r) እውነትን ከፈለግን ለተፈጥሮ ከሚያስፈልገው ሁሉ ውስጥ ለኛ የሚገባውን እንድናይበት እግዚአብሔር በሰጠን ልቡናችን እንፈልጋት። እውነትን (እኛው ተመራምን ነው እንጂ) በሰው ትምህርቶች አናገኛትም፤ ምክንያቱም ሰው ሁሉ ዋሾ ነው።

ከእውነት ይልቅ ውሸትን ብንመርጥ በስሕተታችን የምንጠፋ እኛ ነን እንጂ በዚህ ምክንያት የፈጣሪ ሥርዐትም ሆነ ለፍጥረት ሁሉ የቆመ የባሕርይ ሕግ አይጠፋም። እግዚአብሔር ባቆመው ሥርዐቱ ዓለምን ይጠብቃታል። የሰው (ሕጎች) ሊያጠፏት አይችሉም፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ሥርዐት ከሰው ሥርዐት ያይላል። ስለዚህ (ለምሳሌ) ምንኲስና ከጋብቻ እንዲሻል የሚያምኑ ራሳቸው በፈጣሪ ሥርዐት ኀይል ወደ ወሲብ ይሳባሉ። ጾም ነፍስን እንደሚያጸድቅ የሚያምኑም ረኀብ ሲይዛቸው ይበላሉ። ገንዘቡን የሚጥል ፍጹም እንደሚሆ የሚያምኑም ከገንዘብ በሚገኝ ጥቅም (ምክንያት) ወደገንዘብ ፍለጋ ይሳባሉ። (B, 14v) ከሀገራችን መነኲሴዎች ውስጥ ብዙዎች እንደሚያደርጉት (ገንዘብን) ከተውት በኋላ እንደገና ይፈልጉታል።

በዚህ ሁኔታ ዋሾዎች ሁሉ የተፈጥሮን ሥርዐት ሊያፈርሱ ይሞክራሉ፤ ግን ደካማ ውሸታቸውን ያሳያሉ እንጂ አይችሉም። “ፈጣሪ ታዲያ ይሥቅባቸዋል፤ የፍጥረት ጌታም ይሳለቅባቸዋል።”[51] ምክንያቱም፥ “እግዚአብሔር ፍርድ መፍረድ ያውቃልና። በእጆቹ ሥራ ኀጢአተኛም ይጠመዳል።”[52] በዚህ ምክንያት የጋብቻን ሥርዐት ነውር የሚያደርግ መነኲሴ በዝሙት ወጥመድ፥ ተፈጥሮው ባልሆነ በሌላም የሥጋ ኀጢአት[53] እና በክፉ በሽታ[54] ይጠመዳል።

ገንዘባቸውንም የናቁ (ተመልሰው) ገንዘብ ለማግኘት በነገሥታትና በሀብታሞች ዘንድ (ተጠግተው) ግብዞች ይሆናሉ። ለእግዚአብሔር

---

[51] መዝ 2፡4.
[52] መዝ 9፡16/17.
[53] የተፈጥሮ ባልሆነ ግንኙነት።
[54] በአባለ ዘር በሽታ።

ብለው ዘመዶቻቸውን የሚተዉ በችግራቸውና በእርጅናቸው ጊዜ ረዳት ሲያጡ፥ ከሐሜትና በእግዚአብሔርና በሰው ላይ ክፉ ነገር ከመናገር ይደርሳሉ። በዚህ ሁኔታ የፈጣሪን ሥርዐት የሚያፈርሱ ሁሉ በእጆቻቸው ሥራ ወጥመድ ይገባሉ።

ደግሞ እግዚአብሔር (B, 15r) ስሕተትንና ክፋትን በሰው ማህል ይተዋቸዋል፤ ምክንያቱም ነፍሶቻችን፥ በዚህ ዓለም ልክ የእግዚአብሔር ምርጦች እንደሚፈተኑበት የፈተና ሀገር ውስጥ ስላሉ ነው። ጠቢቡ ሰሎሞን እንዳለው “እግዚአብሔር ጻድቃንን ፈትኖ የእሱ ለመሆን የተገቡ ሆነው አገኛቸው። ወርቅ በምድጃ እንደሚፈተን ፈተናቸው፤ ተቀባይነት እንዳለው እንደ ንጹሕ የሚቃጠል መሥዋዕትም ተቀበላቸው።”[55]

ሞተን ወደፈጣሪያችን ስንመለስ እግዚአብሔር እንዴት ሁሉንም በእውነትና በታላቅ ጥበብ እንዳዘጋጀውና መንገዱ ሁሉ እውነትና ቀጥታ እንደሆነ እናያለን። ሥጋችን ከሞተ በኋላ ነፍሳችን በሕይወት እንደምትኖር ይታወቃል፤ ምክንያቱም ፍላጎታችን በዚህ ዓለም አይፈጸምም። የሌላቸው (የሌላቸውን ነገር) ይፈልጋሉ፤ ያላቸው ባላቸው ላይ ሊጨምሩበት ይፈልጋሉ። ሰው በዓለም ውስጥ ያለውን ሁሉ ንብረቱ ቢያደርግም አይጠግብም፤ እንደገና ይመኛል። ይህ የተፈጥሮ ባሕርያችን ለሚመጣው (ዓለም) ኑሮ ጭምር እንጂ ለዚህ ዓለም ኑሮ ብቻ እንዳልተፈጠርን ያመለክታል። (B, 15v) የፈጣሪያቸውን ፈቃድ የፈጸሙ ነፍሶች እዚያ ፈጽመው ይጠግባሉ፤ በዚያን ጊዜ ምንም ሌላ ነገር አይመኙም። ይኸ ባይኖር የሰው ተፈጥሮ የመጠጠ (የደረቀ) ሆኖ የሚያስፈልገውን ሁሉ ባላገኘም ነበረ።

ደግሞ ነፍሳችን እግዚአብሔርን ማሰብና በኅሊናዋ ማየት ትችላለች። ለዘለዓለም መኖርንም ልታስብ ትችላለች። እግዚአብሔር ይኸንን እንድታስብ (ችሎታውን) በከንቱ አልሰ(ጣት)ም፤ ማሰቡን እንደሰጣት ማግኘቱንም ይሰጣታል እንጂ።

ደግሞ በዚህ ዓለም እውነት ሁሉ አይፈጸምም። ክፉ ሰዎች በዚህ ዓለም ጥሩ ጥሩ ነገር ሲጠግቡ፥ የዋሆች ይራባሉ። የሚደሰት ክፉ አለ፥ የሚያዝን ደግ አለ፤ የሚደላው አመፀኛ አለ፥ የሚያለቅስ እውነተኛ አለ። ስለዚህ ከሞትን በኋላ “ለሁሉም እንደየሥራው የሚከፍልበት”[56] ሌላ ሕይወትና ፍጹም የሆነ ሌላ እውነት

[55] ጥበብ 3፡5-6.
[56] መዝ 61፡13.

ያስፈልጋል። የልቦናቸው ብርሃን የገለጸላቸውን የፈጣሪን ፈቃድ ለፈጸሙና የተፈጥሮዋቸውን የባሕርይ ሕግ ለጠበቁ ዋጋቸውን ይከፍላቸዋል። የተፈጥሮ ሕግ ግልጽ ናት፤ ምክንያቱም ስንመረምር ልቦናችን (B, 16r) በግልጽ ይነግረናል። ግን ሰዎች መመራመር አልፈለጉም። የፈጣሪያቸውን ፈቃድ በእውነት ከመፈለግ ይልቅ በሰው ቃል ማመንን መረጡ።

## ክፍል ስምንት

የፈጣሪ ፈቃድ "ለፈጣሪህ ለእግዚአብሔር ስገድ፤[57] ሰውንም ሁሉ እንደራስህ ውደድ"[58] በሚለን በዚህ አጭር የልቡና አነጋገር እና "(ሰዎች) ባንተ ላይ ሊያደርጉት የማትፈልገውን በሰዎች ላይ አታድርግ፤ ሊያደርጉልህ የምትፈልገውን ሁሉ አድርግላቸው"[59] በሚለው የልቡናችን አነጋገር ይታወቃል።

ደግሞ የኦሪት ዓሥሩ ቃላት፥ ሰንበትን ስለማክበር በተቀር፥ የእግዚአብሔር ፍላጎት ናቸው፤[60] ምክንያቱም ስለሰንበት ማክበር ልቡናችን ዝም ይላል። እንዳንገድል፤ እንዳንሰርቅ፥ እንዳንዋሽ፥ ወደሰው ሚስት እንዳንሄድና (እነዚህን) ስለሚመስለው (ከሆነ እውነትም) ልናደርጋቸው የማይገባን እንደሆነ ልቡናችንም ያስተምረናል። ስድስቱ ቃላተ ወንጌልም እንደዚሁ የፈጣሪ ፍላጎት ናቸው፤[61] ምክንያቱም ይኸንን የምሕረት ሥራ ሌሎች እንዲሠሩልን እንፈልጋለን፤ ለሌሎችም የሚቻለንን ልናደርግ ይገባናል።

(B, 16v) ደግሞ በዚህ ዓለም ሕይወታችንንና ኑሯችንን እንድንንከባከብ የፈጣሪ ፍላጎት ነው፤ ምክንያቱም በፈጣሪ ፍላጎት መጥተናልና በዚህ ሕይወት እንኖራለን፤ በቅዱስ ፈቃዱ ካልሆነ ልንተወው አይገባም። ንብረታችንንም በዕውቀታችንና በሥራ እንድናሣምረው እሱ ፈጣሪያችን ይፈልጋል፤ ምክንያቱም ለዚህ የሚሆን ልቡናና ችሎታ ሰጥቶናል።

---

[57] ማቴ 4፡9. ጥቅስ ቢሆንም፥ የሚያቀርበው ተመራምሮ እንደደረሰበት ነው።
[58] ማቴ 19፡19. ጥቅስ ቢሆንም፥ የሚያቀርበው ተመራምሮ እንደደረሰበት ነው።
[59] ማቴ 7፡12. ጥቅስ ቢሆንም፥ የሚያቀርበው ተመራምሮ እንደደረሰበት ነው።
[60] ዘፀ 20፡1-17.
[61] ማቴ 5፡3-11.
[62] የሚቃወመው ተግባረ እድን የሚያዋርደውን ባህል ነው።

ስለዚህ የእጅ ሥራም የፈጣሪ ፍላጎት ነው፤ ምክንያቱም ያለ (ተግባረ እድ) ለሕይወታችን የሚያስፈልገን አይገኝም።[62]

አንዱ ከአንዲቷ ጋራ መጋባትና ልጆች ማሳደግም እንዲሁ ነው።

ደግሞ ከልቦናችን ጋራ የሚስማሙ፥ ለሕይወታችን ወይም ለሰው ልጅ ሁሉ ንብረት የሚያስፈልጉ፥ ብዙ ሌሎች ሥራዎችም አሉ። ልንጠብቃቸው ይገባል፤ ምክንያቱም የፈጣሪያችን ፍላጎት እንደዚህ ነውና። እግዚአብሔር አስተዋዮችና የተሟላን ሆነን ፈጣሪያችን በጥበቡ ላዘጋጀልን ዋጋ የተገባን እንድንሆን በዚህ ዓለም ባለንበት ጊዜ ለማሟላት አስተዋዮችና ዝግጁዎች አድርጎ እንድንሟላ ፈጠረን እንጂ የተሟላን አድርጎ እንዳልፈጠረን ልናውቀው ይገባናል።

(B, 17r) እግዚአብሔር የተሟላን አድርጎ ሊፈጥረንና በምድርም ላይ ብፁዓን ሊያደርገን ይቻለው ነበረ። ግን እንዲህ አድርጎ ሊፈጥረን አልፈለገም። ለመሟላት ዝግጁዎች አድርጎ ፈጥሮ ከሞትን በኋላ ፈጣሪያችን ለሚሰጠን ዋጋ የተሟላንና የተዘጋጀን እንድንሆን በዚህ ዓለም ፈተና መካከል አስቀመጠን። በዚህ ዓለም እስካለን ድረስ ፈጣሪያችንን ልናመሰግነው፥ ፈቃዱን ልንፈጽም፥ ወደሱ እስኪወስደን ድረስ ልንታገሥ፥ የፈተናችን ዘመንም እንዲያቀልልን፥ ኀጢአታችንንና ባለማወቅ የሠራነውን ሞኝነት (ሁሉ) ይቅር እንዲለን፥ የተፈጥሯችንን ሕጎች ዐውቀን እንድንጠብቃቸው ልቡና እንዲሰጠን ቸርነቱን ልንለምን ይገባናል።

ስለጸሎትም ሁልጊዜ ልንጸልይ ይገባል፤ ምክንያቱም (ጸሎት) ለአስተዋይ ፍጥረት ተከታይዋ ነው። ሁሉን የሚያውቅ፥ ሁሉን የሚጠብቅ፥ ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር እንዳለ የምታስተውል አሳቢ[63] ነፍስ (B, 17v) እንድትጸልይና ከሱ ደግ ነገሮች አንድትለምን፥ ከክፉ ነገር እንድትድንም ወደሱ ትሳባለች። ሁሉን በሚችልና የሚያቅተው ምንም ነገር በሌለው እግዚአብሔር እጅ ትማፀናለች። እግዚአብሔር ታላቅና ልዑል ነው፤ ከበታቹ ያለውን ያያል፤ ሁሉን ይይዛል፤ ሁሉን ያስተውላል፤ ሁሉን ይመራል፤ ሁሉን ያስተምራል። ችግራችንን ሁሉ የሚያውቅ አባታችን፥ ፈጣሪያችን፥ ጠባቂያችን፤ የነፍሳችን ዋጋ፥ መሐሪ፥ ቸር ነው። በትዕግሥታችን ይደሰታል፤ የፈጠረን ለሕይወት እንጂ ለጥፋት አይደለም።

---

[63] "Rational."

ጠቢቡ ሰሎሞን እንዳለው፥ "ጌታ ሆይ፥ አንተ ሁሉን ትምራለህ[64]፤ አንተ በማንም ላይ ችሎታ አለህና ለንስሐ ለማብቃት የሰውን ኀጢአት ትንቃለህ፤ (በሕይወት) ያለውን ሁሉ ትወዳለህ፤ ከፈጠርከው ምንም የምትንቀው የለም። ፍጥረትን ሁሉ ትምራለህ ትራራለታለህም።"[65] እግዚአብሔር አስተዋዮች አድርጎ የፈጠረን ታላቅነቱን እንድናስብ፥ እንድናመሰግነውም ለሥጋችንና ለነፍሳችን የሚያስፈልገንን ለማግኘት ወደሱ እንድንጸልይ ነው። ፈጠሪያችን በሰው ልብ ያስቀመጠው ልቡናችን ይኸንን ሁሉ ያስተምረናል። (ይኸ) እንዴት ከንቱና ውሸት ይሆናል?

## ክፍል ዘጠኝ

ደግሞ በሙሉ ልባችን በፍቅር፥ በእምነት፥ በትዕግሥት ስንጸልይ ጸሎታችንን እግዚአብሔር እንደሚሰማ በሌላ መንገድ አወቅሁ፤ ምክንያቱም እኔ ራሴ ኀጢአተኛ ነኝ፤ ከልጅነቴ ጀምሮ ለብዙ ዘመን ስለእግዚአብሔር ሥራ ምንም ሳላስብ፥ ወደሱም ሳልጸልይ እኖር ነበረ። ለአስተዋይ ፍጥረት በማይገባት (መንገድ) ብዙ አጠፋሁ። በኀጢአቴም ምክንያት ሰው ሊያመልጣት ከማይችል ወጥመድ ወደቅሁ፤ ፈጽሞ ልበላሽም ደረስኩ። "የሞት ድንጋጤም መጣብኝ።"[66] በዚያች ጊዜ ወደእግዚአብሔር ተመለስኩና እንዲያድነኝ ወደሱ መጸለይ ጀመርኩ፤ ምክንያቱም እሱ የመዳኛ መንገዶችን ሁሉ ያውቃል። ለእግዚአብሔር (እንዲህ) አልኩት፤ "ከኀጢአቶቼ እመለሳለሁ፤ ጌታ ሆይ፥ ፈቃድህንም ፈልጌ እፈጽማታለሁ። ብቻ አሁን ኀጢአቴን ይቅር ብለህ (B, 18v) አውጣኝ።" (እንደዚህ እያልኩ) በሙሉ ልቤ ለብዙ ጊዜ ጸለይኩ። እግዚአብሔር ሰማኝ፥ ፈጽሞም አዳነኝ። አመስግኜው ወደሱ በፍጹም ልቤ ተመለስኩ። በመዝሙር 114 (ቃል)፥ "እግዚአብሔር የልመናዬን ቃል ስለሰማኝ ወደድኩት"[67] አልኩ። ይህ መዝሙር ለኔ የተደረሰ መሰለኝ። ደግሞ፥ "እድናለሁ እንጂ አልሞትም፤ የእግዚአብሔርን ሥራም እናገራለሁ"[68] አልኩ።

---

[64] ጥቅሱ የሚለው "ትምሕር" (ትምራለህ) ነው። የተቀዳው ግን በስሕተት "ትሜህር" (ታስተምራለህ) ተብሎ ነው።
[65] ጥበብ 11፡24-27.
[66] መዝ 54፡5.
[67] መዝ 114፡1.

ደግሞ ሁልጊዜ በውሸት የሚከሱኝ ነበሩ፤ ከንጉሡ ዘንድ (ሄደው)፥ “ይኸ ሰው ጠላትህ ነው፤ የፈረንጆቹም ጠላት ነው” አሉት። የንጉሡ ቁጣም በላዬ ላይ እንደነደደ አወቅሁ። ከዕለታት በአንዱ ቀን የንጉሡ ሹመኛ ወደኔ መጣና፥ “ንጉሡ ወደኔ ቶሎ ና ይልሃል” አለኝ። እኔም በጣም ፈራሁ፤ ልሸሽ ግን አልተቻለኝም፤ ምክንያቱም የንጉሡ ሰዎች ይጠባበቁኝ ነበረ። ሌሊቱን በሙሉ ባዘነ ልቤ ጸለይኩ። ጠዋት ተነሥቼ ሄድኩና ከንጉሡ ዘንድ ቀረብኩ። እግዚአብሔር (B, 19r) የንጉሡን ልብ አራርቶት በፍቅር ተቀበለኝ። ስለፈራሁት ነገር ምንም ምን አላለም። ግን ስለ ብዙ የትምህርት ጉዳይና ስለመጻሕፍት ጠየቀኝ። (እንዲህም) አለኝ፥ “አንተ ምሁር ሰው ስለሆንክ ፈረንጆቹን ልትወዳቸው ይገባል፤ ምክንያቱም እነሱ በጣም ምሁሮች ናቸው።” “እሺ” አልኩት፤ ምክንያቱም ፈርቼ ነበረ፤ ፈረንጆቹም እውነትም በጣም ምሁሮች ነበሩ። ከዚህ በኋላ ንጉሡ አምስት ወቄት ወርቅ ሰጥቶ በሰላም አሰናበተኝ። ከንጉሡ (ግቢ) ወጥቼ፥ ደግ ሥራ የሠራልኝን እግዚአብሔርንም አደነቅሁ፥አመሰገንኩትም።

ወልደ ዮሐንስ ደግሞ (እንደገና) በውሸት ሲከሰኝ ግን ሸሸሁ እንጂ (እግዚአብሔር) እንዲያድነኝ እንደበፊተኛው አልጸለይኩም፤ ምክንያቱም ለመሸሽ ተችሎኝ ነበረ። ሰው እግዚአብሔርን በከንቱ ሳይፈታተነው[69] የሚቻለውን ሁሉ (ራሱ) መሥራት ይገባዋል። አሁን ግን አመሰግነዋለሁ፤ ምክንያቱም ሽሽቴ ከዋሻዬ በመኖሬ በፍጹም (ልቤ) ወደ (B, 19v) ፈጣሪዬ ተመልሼ በፊት ያላሰብኩትን እንዳስብና ነፍሴን ታላቅ ደስታ የሚያስደስታት እውነትን እንዳውቅ ምክንያት አግኝቻለሁና። በእውነት እግዚአብሔርን “ቅጣትህን አውቅ ዘንድ ያሳመምከኝ የሚገባኝ ነው”[70] እለዋለሁ፤ ምክንያቱም ብቻዬን በዋሻዬ ውስጥ በነበርኩ ጊዜ ከመምህራን ጋራ ባለሁበት ጊዜ ከተረዳሁት ይበልጥ ተረድቻለሁ። እዚህ የጻፍኩትም በጣም ጥቂቱን ነው።

ይኸንን የሚመስል በብዙው እያሰብኩ እዋሻዬ ውስጥ ኖርኩ። ጥበብና የተፈጥሮን ምስጢሮች መረዳትን የሰጠኝን እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ። ነፍሴ ሁሉንም ጥላ የእግዚአብሔርን ሥራና ጥበቡን ብቻ እያሰበች ወደሱ ትሳባለች። ሁል ጊዜ በሙሉ ልቤ በመዝሙረ ዳዊት ጸለይኩ፤ ምክንያቱም ይኸ ጸሎት በጣም ይጠቅመኛል።

[68] *መዝ* 117፡17.
[69] *ማቴ* 4፡7.
[70] *መዝ* 118፡71.

ኀሊናዬንም ወደ እግዚአብሔር ከፍ ያደርገዋል። መዝሙረ ዳዊት ውስጥ ከኀሊናዬ ጋራ የማይስማማ ሳገኝ እኔ ተርጕሜ በዕውቀቴ አስማማውና ሁሉም ጥሩ ይሆንልኛል።

እንደዚህ ስጸልይ በእግዚአብሔር ላይ ያለኝ መተማመን ይበዛል። (B, 20r) ሁል ጊዜ፥ "ጌታ ሆይ፥ ጸሎቴን ስማልኝ፤ ልመናዬንም አትናቅብኝ።"[71] "ከሰው ልጅ ኀይልም አድነኝ።"[72] "አንተ ጌታ ሆይ፥ ምሕረትህን ከኔ አታርቅ። ምሕረትህና እውነትህ ሁል ጊዜ ያግኙኝ።"[73] አቤቱ ጠርቸሃለሁና አልፈር።"[74] "እንደዚህ እየለመንኩህ ዘላለም እዘምራለሁ። ምኞቴን ሁል ጊዜ ትሰጠኝ ዘንድ።"[75] "ወደኔ ተመልከትና ማረኝ። ለባርያህ ኀይል ስጠው። የገረድህን ልጅም አድነው። የደግ (ነገር) ምልክት እኔ ላይ ሥራ።"[76] ስለስምህ ምራኝ፤ መግበኝም።"[77] ነፍሴን ከኃጥአን ጋራ አትሳባት።"[78] "በአንተ ላይ የተማመንኩትን ያህል ምሕረትህ በኔ ላይ ትሁን።"[79] "የሚሰማ ምሕረትህን በጠዋት አድርግልኝ።"[80] ጠብቀህ በምድር ላይ ደስተኛ አድርገኝ። "ከጠላቶቼ እጅ አታግባኝ።"[81] "ደስታና እሰይታን አሰማኝ።"[82]" ከተስፋዬ አታሳፍረኝ።"[83] "እነሱ ይረግማሉ አንተ ባርክ።"[84] "ይህቺ እጅህ እንደሆነች ይወቁ።"[85] ይኸንንና የመሰለውን በሙሉ ልቤ ቀንና ሌሊት እጸልያለሁ።

---

[71] መዝ 54፡2.
[72] መዝ 118፡134.
[73] መዝ 39፡12.
[74] መዝ 30፡18.
[75] መዝ 60፡9.
[76] መዝ 85፡16-17.
[77] መዝ 30፡4.
[78] መዝ 27፡3.
[79] መዝ 32፡22: "በአንተ ላይ የተማመንነውን ያህል ምሕረትህ በእኛ ላይ ትሁን።"
[80] መዝ 142፡8.
[81] መዝ 40፡2/3 ዳዊት የሚለው "ወኢያገብአ ውስተ እደ ጸላኢሁ" (እጠላቱ እጅ አያገባውም) ነው።
[82] መዝ 50፡ 10: ታሰምዐኒ . . .
[83] መዝ 118፡ 116.
[84] መዝ 108፡28.
[85] መዝ 108፡27.

## ክፍል ዓሥር

ጠዋትና ማታ የምጸልየው ጸሎት እንደዚህ ነው፤

(B, 20v) ፈጣሪዬና ጠባቂዬ ሆይ፥ እሰግድልሃለሁ። በሙሉ ልቤም አፈቅርሃለሁ። በዚች ሌሊት ስለሠራህልኝ ጥሩ ጥሩ ነገር አመሰግንሃለሁ።

ማታ ደግሞ (እንዲህ) እላለሁ፤

በዚህ ቀን ጠብቀኝ፤ በዚች ቀንም እንዲሁ።

ማታ ደግሞ (እንዲህ) እላለሁ፤

በዚች ዕለትና በሕይወቴ እድሜ ሁሉ በኔ ላይ ያለህን ፈቃድህን አውቅና እፈጽመው ዘንድ በዚች ሌሊት ግለጽልኝ። ኀጢአቶቼንም ይቅር በልልኝ። ለሕይወት የሚያስፈልገውን የሚበቃውን ያህል ሁል ጊዜ ስጠኝ። በአንተ ላይ ያለኝን መተማመን ሁልጊዜ አጽናልኝ። ጌታዬ ሆይ፥ በቸርነትህ፥ በኀይልህ፥ በትልቅነትህም ከምስኪንነት፥ ከሰው እጅና መላስ፥ ከሥጋ በሽታ፥ ከነፍስ ሐዘን፥ አድነኝ።

ከዚህ በኋላ "ባንተ ተወከልኩ" (ብሎ በሚጀምረው) በመዝሙር 30 እጸልያለሁ፤

አስቤም (እንዲህ) አልኩ፤ "ለሕይወቴ የሚያስፈልገኝን ሁሉ ለማግኘት በችሎታዬ ሁሉ መሥራትና መድከም አለብኝ። ጸሎት ብቻውን አይበቃኝም።" ግን ሥራ ስለማላውቅ ወደ እግዚአብሔር ኀይል እመለሳለሁ፤ "ጌታ ሆይ፥ ያላንተ በረከት ሥራዬ ምንም ምን አይጠቅመኝም። (B, 21r) አንተ አሳቤን፥ ሥራዬን ኑሮዬን ባርክ (ልኝ)። ገንዘብና ደስታ አንተ በምታውቀውና በምትፈቅደው መንገድ ስጠኝ። ከኔ ጋራ ያሉ ሰዎች ደግ እንዲሠሩልኝ ልባቸውን ለውጠ(ው)፤ ሁሉም በቡሩክ ፈቃድህ ይሆናልና። የሽምግልና ጊዜዬንም አሳምርልኝ።"

ልባችን ሁልጊዜ በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ እንደሆነ አወቅሁ። እግዚአብሔር በችግር፥ በድኽነት፥ በሕመም ላይም በምንሆንበት ጊዜ እንኳን ብፁዓንና ደስተኞች ሊያደርገን ይችላል። ደግሞ በሀብት ማህልና በዚህ ዓለም ድሎት ሁሉ መካከልም ችግረኞች ሊያደርገን ይችላል። ስለዚህ ሁል ጊዜ ድኾችና ምስኪኖች በልባቸው (ውስጥ በሠረፀ) ደስታ ሲጫወቱ፥ ሀብታሞችና ንጉሦች በሀብታቸው በምኞታቸው ብዛት መካከል ሲያዝኑና ሲበሳጩ እናያቸዋለን። ኀዘን

እኛ ሳንፈቅድ፥ የገባበትን ምክንያትም ሳናውቅ፥ ከልባችን ይገባል። ደስታና እሰይታ እንዲያሰማንና በምድር ላይ ብፁዓን እንዲያደርገን ወደ እግዚአብሔር ልንጸልይ ይገባናል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለእውነተኞች ብርሃንን፥ ለልበ ቀናዎች ደስታን ያንጸባርቃል።[86] (B, 21v) እሱ የልባችንን መንገድ ሁሉ ያውቃል፤ ይገዛልም። በችግራችን ውስጥ ደስተኞች፥ በጥሩ ጥሩ (ነገሮች ውስጥ) ሐዘንተኞች ሊያደርገን ይችላል። ምክንያቱም ደስታና ሐዘን እግዚአብሔር እንደሚያሰማን እንጂ ለሰዎች እንደሚመስላቸው አይደርሱብንም።

(እንደዚህም) አልኩ፤ “አንተ ጌታዬና ፈጣሪዬ ነህ፤ ደስታና እሰይታን አሰማኝ፤ በምድር ላይ እስካለሁ ድረስ ብፁዕ አድርገኝ፤ ከሞቴም በኋላ ወዳንተ ውሰደኝ፤ በአንተም አጥግበኝ።”

እንደዚህ ቀንና ሌሊት እየጸለይኩና በየሥርዐታቸው (ያሉትን) የእግዚአብሔርን ሥነ ፍጥረቶች እያደነቅሁ ኖርኩ። እንሳሳዎችና የዱር አውሬዎች፥ እነሱም በተፈጥሯቸው ባሕርይ ሕይወታቸውን ወደመጠበቅና ዘራቸውን ወደማኖር ይሳባሉ። በታላቅ ጥበብ የተፈጠሩ የዱር ዛፎችና ሣርም ይበቅላሉ፤ ይለመልማሉ፤ ያብባሉ፤ በየዘራቸውና በየወገናቸው ያለስሕተት ፍሬ ያወጣሉ፤ ነፍስ ያለባቸው ይመስላሉ። ደግሞ ተራሮችና ቆላዎች፥ ወንዞችና የውሐ ምንጮች (እንዲሁ ናቸው)። (B, 22r) “ጌታ ሆይ፥ ሥራህ ሁሉ ስምህን ያመሰግናል፤ ስምህ በምድር ሁሉ በጣም ተመሰገነ።[87] በሰማይም የጆችህ ሥራ በጣም ትልቅ ነው። ይህ ፀሐይ የብርሃን ምንጭና የዓለም ሕይወት ምንጭ ነው። አንተ የሰቀልካቸው ጨረቃና ኮከቦችም የሠራህላቸውን መንገድ የማይስቱ ናቸው። የኮከቦችን ቍጥር፥ ርቀታቸውን፥ ስለርቀታቸው ትናንሽ የሚመስሉን ትልቅነታቸውን ማን ያውቃል? ደመናዎችም ልምላሜ የሚያበቅሉ ውሐዎችን የሚያወርዱ ናቸው። ሁሉም ታላቅና ግሩም ነው፤ ሁሉም በጥበብ ተሠርቷል።

እንደዚህ ሳደንቅና ፈጣሪን ሳመሰግን ሁለት ዓመት ኖርኩ።

አስቤም (እንዲህ) አልኩ፤ የእግዚአብሔር ሥራ በጣም ጥሩ ነው፤ ሐሳቡ ጥልቅ፥ ጥበቡም የማይነገር ነው። ታዲያ እንዴት አንድ ትንሽና

[86] መዝ 96፡11.
[87] መዝ 8፡2፤ 8፡10.

ምስኪን ሰው[88] ዋሽቶ፥ "ጥበቡንና እውነቱን ለሰው እገልጽ ዘንድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላክሁ" ይላል? ከከንቱ ነገር፥ ከሚናቅ፥ ትልቅነቱን እንድንረዳ ፈጣሪ ከሰጠን ኅሊና በጣም ዝቅተኛ ከሆነ ባሕርዩ በቀር (ሌላ ምንም) አይገልጥልንም።

(እንዲህም) አልኩ፤ ጌታ ሆይ፥ እኔ በፊትህ ደኻና ምስኪን ነኝ። (B, 22v) ትልቅነትህን አደንቅና ሁል ጊዜ "አዲስ ምስጋና"[89] አመሰግንህ ዘንድ ስላንተ ላውቅ የሚገባኝን ግለጽልኝ።

## ክፍል ዓሥራ አንድ

ንጉሥ ሱስንዮስ በ1625 ዓመተ ምሕረት ሞተ። በምትኩ ልጁ ፋሲለደስ[90] ነገሠ። በመጀመሪያው ላይ እሱም እንደአባቱ ፈረንጆቹን ወድዶ ነበረ። ሆኖም ግብጻውያንን አላሳደዳቸውም፤ በኢትዮጵያ ሀገሮች ሁሉ ሰላም ሰፈነ።

በዚያን ጊዜ ከዋሻዬ ወጥቼ ወደ አምሐራ አገሮች ሄድኩ፤ በኋላ ወደ ቤገምድር ተሻገርኩ። ፈረንጆችን ለሚጠሉ ሁሉ በሱስንዮስ ዘመን ከሸሹ መነኮሳት አንዱ መሰልኳቸው። በዚህ ምክንያት ወደዱኝ፤ ምግብና ልብስም ሰጡኝ።

እንደዚህ ከሀገር ወደ ሀገር ስሄድ ወደአክሱም ለመመለስ አልፈለግሁም፤ ምክንያቱም የካህናቷን ክፋታቸውን አውቅ ነበረ። የሰው ሂደት በእግዚአብሔር እንደሚጸናም አስታወስኩ፤ (እንዲህም) አልኩ፤ "ጌታ ሆይ፥ የምሄድበትን መንገድ እና የምኖርበትን ሀገር ምራኝ።"[91] ወደጐዣም ተሻግሬ (B, 23r) (እዚያ) እንድኖርም አሰብኩ። እግዚአብሔር ግን ወደ አላሰብኩበት መራኝ።

ከዕለታት በአንዱ፥ እንፍራዝ (ውስጥ) ሀብቱ፥ ማለት፥ ሀብተ እግዚአብሔር፥ ከሚባል አንድ ሀብታም ሰው ዘንድ ደረስኩ። እዚያ

---

[88]ነቢይ። ኢየሱስ ክርስቶስን ግን እንደ ሙሴና እንደ መሐመድ ስሙን አንሥቶ አይነቅፈውም።

[89]መዝ 32፡3፤ 95፡1፤ 97፡1፤ 149፡1፤143፡9.

[90]ለቀጂው "ፋሲለደስ" ሰማዕት እንጂ፥ ኢትዮጵያ እንዲህ ያለ ንጉሥ አልነበራትም። "ፋሲለደስ" የተባለው "ፋሲል" መሆኑን ስለማያውቅ፥ የነገሠው ወልደ ፋሲለደስ መስሎት፥ "ወልዱ" (ልጁ) የሚለውን "አርሞ" ወይም መስሎት "ወልደ ፋሲለደስ" ብሎታል።

[91]መዝ 142፡8: ምርሐኒ እግዚኦ ፍኖተ እንተ ባቲ አሐውር።

አንድ ቀን ቆይቼ፥ በማግስቱ አክሱም ላሉ ዘመዶቼ ደብዳቤ እንድጽፍ ቀለምና ክርታስ[92] ለመንኩት። ሰውየው፥ "ጸሐፊ ነህ ወይ?" አለኝ፤ "አዎን፥ ጸሐፊ ነኝ" አልኩት። መልሶ፥ "ከኔ ጋራ ጥቂት (ጊዜ) ተቀመጥና መዝሙረ ዳዊት ቅዳልኝ፤ ዋጋህን እሰጥሃለሁ" አለኝ። "እሺ" አልኩት። የድካሜን ፍሬ የምበላበትን መንገድ ያሳየኝን እግዚአብሔርን በልቤ ውስጥ አመሰገንኩት፤ ምክንያቱም ወደቀድሞው መምህርነቴ መመለስን ጠልቼ ነበር፤ ውሸት ማስተማርም አልፈለኩም። እውነቱን ባስተምር ሰዎች ይጠሉኛል እንጂ አይሰሙኝም፤ በውሸት ከሰውም ያሳድዱኛል። እኔ ግን ከሰው ሁሉ ጋራ በሰላምና በፍቅር መኖርን፥ በኀጢአተኞች ቤት ከብሬ ከመኖር ይልቅ የድካሜን ፍሬ እየበላሁ ከሰው ተረስቼ፥ (B, 23v) ተደብቄ እግዚአብሔር በገለጸልኝ ጥበብ መኖርን እመርጣለሁ።

በጥቂት ቀናት ውስጥ ቀለምና ክርታስ አዘጋጅቼ አንድ የመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ ቀዳሁ። ጌታ ሀብቱና ጽሕፈቴን ያዩዋት ሁሉ አደነቁ፤ ምክንያቱም ጥሩ ነበረች። ጌታ ሀብቱ ዋጋዬን አንድ ጥሩ ልብስ ሰጠኝ። ከዚያ በኋላ የዚህ የሀብቱ ልጅ ወልደ ሚካኤል፥ "ለአባቱ እንደጻፍክለት ለኔም ጻፍልኝ" አለኝ። ጻፍኩ(ለት)፤ አንድ ላምና ሁለት ፍየል ሰጠኝ። ከዚህ በኋላ ብዙዎች ወደኔ እየመጡ መጽሐፈ ዳዊትና ሌሎችም መጽሐፎች ደብዳቤዎችም አስጻፉ። ምክንያቱም በዚህ ሀገር ከኔ በቀር ሌላ ጸሐፊ የለም። ልብሳ ልብስ፥ ፍየል፥ ጨው፥ እህል እና የመሰለውን ሰጡኝ።

ጌታ ሀብቱ ሁለት ሕፃናት ልጆች አሉት፤ (ስማቸው) የአንዱ ተሰማ የተባለው ወልደ ገብርኤል፥ የሁለተኛው ምትኩ የተባለው ወልደ ሕይወት ነው። አባታቸው (B, 24r) ሀብቱ፥ "የዳዊት ንባብ አስተምራቸው፤ ዋጋህን የሚበቃህን ምግብ እሰጥሃለሁ፤ በእጅህ ጽሕፈት የምታፈራው ያንተ ይሆናል" አለኝ። "እሺ፥ አባቴ ሆይ፥ ያዘዝከኝን ሁሉ አደርጋለሁ። ብቻ በአባቴ፥ በእናቴ፥ በዘመዶቼ ምትክ ሁንልኝ፤ ምክንያቱም ያላንተ ዘመድ የለኝም" አልኩት።

## ክፍል ዓሥራ ሁለት

ወንድ ሚስት ሳትኖረው ብቻውን ይኖር ዘንድ እንደማይገባው አወቅሁ፤ ምክንያቱም ይህ (የብቸኝነት) ኑሮ ወደ ኀጢአት ይስባል።

[92] ስሌዳ "ብራና" መሆን አለበት።

ሰዎች በሚሠሩት መጥፎ ሥራቸው እንዳይጠመዱ ተፈጥሯቸው ባልሆነ ኑሮ (ለምሳሌ በምንኩስና) ይኖሩ ዘንድ አይገባቸውም። ለቀድሞዎቹ እንደተባለ፥ "ወንድ ብቻውን ቢኖር ጥሩ አይደለም"፤[93] ሚስት ይፈቀድለታልና።

ለጌታ ሀብቱ (እንዲህ) አልኩት፤ "በክፉው ዘመን ምክንያት መነኩሴ መሰልኩ እንጂ (መነኩሴ) አይደለሁም።" የጌታ (ሀብቱ) አገልጋይ የሆነች ኂሩት የምትባል ሴት ልጅ ነበረች። ቆንጆ አይደለችም፤ ግን ባለ ጥሩ ጠባይና አስተዋይ ናት። ጌታ ሀብቱን (እንዲህ) አልኩት፤ "ይችን ልጅ ሚስት እንድትሆነኝ ስጠኝ።" ጌታ ሀብቱም፥ "እሺ፥ ካሁን ጀምሮ (B, 24v) አገልጋይህ እንጂ አገልጋዬ አይደለችም" አለኝ። እኔም፥ "አገልጋዬ ሳይሆን ሚስት ትሁነኝ፤ ምክንያቱም በጋብቻ ወንድና ሴት እኩል ናቸው፤ ጌታና አገልጋይ ልንላቸው አይገባም፤ ምክንያቱም (ሁለቱ) አንድ አካል፥ አንድ ንብረት ናቸው" አልኩት። ጌታ ሀብቱም፥ "አንተ የእግዚአብሔር ሰው ነህ፤ እንደፈለግህ አድርግ" አለኝ።

ያችን ልጅ ጠራትና፥ "ሚስቴ እንድትሆኚ ፈቃድሽ ነውን?" አልኳት። "እንደ ጌታዬ ፈቃድ ይሁን" አለችኝ። ጌታ ሀብቱ፥ "እኔ እፈቅዳለሁ" አላት። እሷም፥ "ለኔ ጥሩ ነው፤ ካንተ የሚሻለኝን ከየት አገኛለሁ?" አለችኝ።

ጌታ ሀብቱን፥ "አባታችን ሆይ፥ ባርከን" አልነው። "እግዚአብሔር ይባርካችሁ፤ ይጠብቃችሁ፤ ለረጅም ዘመን ጤናና ፍቅር ይስጣችሁ፤ ልጆች ከዚህ ዓለም ሀብት ጋራ ይስጣችሁ፤ ክፉ ነገርን ከናንተ ያርቅ" አለ። "አሜን፥ አሜን" አልን።

ይህቺ ኂሩት ሚስቴ ሆነች። በጣም አፈቀረችኝ። ብዙ ደስታም ተደሰተች፤ ምክንያቱም በፊት በሀብቱ ቤት የተናቀች ነበረች፤ የቤቱ ሰዎችም ሁልጊዜ ያንገላቷት ነበረ። (B, 25r) እኔም ስለወደደችኝ በተቻለኝ ሁሉ እንዳስደስታት በልቡናዬ አሳደርኩ። እንደኛ ጋብቻ በፍቅር የጸናና በእግዚአብሔር የተባረከ ሌላ ጋብቻ እንደሌለ ታዘብኩ።

ከአክሱም በሸሸሁ ጊዜ ወስጀው ከነበረ የተረፈ ሁለት ወቄት ወርቅ ነበረኝ። በእጄ ጽሕፈት ከብቶች፥ ፍየሎች፥ ልብሳ ልብስ አተረፍኩ።

---

[93]ዘፍ 2፡18.

ከጌታ ሀብቱ ጐረቤት ትንሽ ቤት ሠራሁ። እዚያ ከሚስቴ ጋራ በፍቅር ኖርኩ። እሷ ቀንና ሌሊት ትፈትላለች፤ እኔ እጽፋለሁ፥ የሀብቱንና እዚያ ያሉትን ልጆች አስተምራለሁ። ጌታ ሀብቱ ልጆቹን ስለማስተምራቸው በየወሩ አንድ እንስራ ጤፍ ይሰጠኛል።

እንደዚህ ከሚስቴ ጋራ በፍቅርና በጥሩ ኑሮ ሁለት ዓመት ኖርኩ። ልጅ ግን አልወለደችልኝም። ከዚህ በኋላ ፀነሰችና ጥቅምት 11 ቀን፥ ሰኞ ዕለት ከክርስቶስ ልደት በ1631 (ዓመት) ወንድ ልጅ ወለደች። በልጃችን ተደሰትን። የጸጋ አባቴ በሆነው (ሰው) ስም ሀብተ (B, 25r) እግዚአብሔር አልኩት።

ከሶስት ዓመት በኋላ አቡነ እፍንስ አገሩ ሄደ። ጠላቶቹ ሁሉም ከፍ ከፍ አሉ፤ ወዳጆቹ ግን አብረውት ተሰደዱ። በዚያን ጊዜ የጥንቱን ትምህርት የሚያስተምሩና የሚያጸኑ መምህራን ተፈለጉ። በአክሱም ያሉ ዘመዶቼም ወደ መምህርነቴ ተመልሼ አክሱም ውስጥ እንደቀድሞው መጻሕፍት እንዳስተምር ፈለጉኝ፤ ምክንያቱም ሰዎች በአቡነ እፎንስ ምክንያት ስደት ፈርቼ የሸሸሁ መስሏቸዋል። (እንዲህ) ሲሉ ላኩብኝ፤ "ወደኛ ተመለስ፤ ምክንያቱም ጠላቶችህ ጠፍተዋል፤ ወዳጆችህም ድነዋል።" (እንዲህ) ብዬ መለስኩላቸው፤ "ጠላትም የለኝም፤ ከዚህ ከእግዚአብሔር ሰው ከጌታዬ ሀብቱ፥ ከልጆቹ፥ ከሚስቴ ሌላ ወዳጅም የለኝም፤ እነሱን ፈጽሞ አልተዋቸውም። እናንተም በሰላም ኑሩ። እኔ ግን ወደናንተ እመለስ ዘንድ አይሆንልኝም።"

ያ፥ ካሁን በፊት ከንጉሥ ሱስንዮስ ዘንድ በውሸት የከሰሰኝ ግብዝ ጠላቴ ወልደ ዮሐንስ፥ አቡነ እፎንስ ከሄደ በኋላ ወደ ግብጾቹ ሃይማኖት ተመለሰ። ግን ለጊዜው የሚሻለውን (መያዙ) ነው እንጂ ሃይማኖትስ የለውም። (B, 26r) ከሸንጋይነቱ ብዛት ሄዶ የንጉሥ ፋሲለደስ ወዳጅ ሆነ። ምክንያቱም ነገሥታት ሸንጋዮችንና ግብዞችን ይወዳሉ። በብሔረ እንፍራዝ በሰላም እንዳለሁ ሰምቶ፥ "በድብቅ የፈረንጆችን ትምህርት የሚያስተምር የፈረንጅ መምህር ነው" እያለ እንደገና በውሸት ይከሰኝ ጀመር። ይኸንንም ለእንፍራዙ ሹም ነገረው። እኔም በሸንገላው በጣም አዘንኩ፤ ምክንያቱም ስለኔ ከዚህ በፊት የፈረንጆች ጠላት ነው ብሎ ነበረ፤ በኋላ ደግሞ ወዳጃቸው ነው አለ(ኝ)። በልቤ ሐዘንም (እንዲህ) አልኩ፥ "እግዚአብሔር የብልሹ ከንፈሮችን ይነቅላል"።[94] "ግፉቸው" (ብሎ በሚጀምረው) በመዝሙር

94 መዝ 11፡4.

34 እና "አቤቱ እምቢ አትበለኝ (ብሎ በሚጀምረው) በመዝሙር 108 ለብዙ ዘመን ጸለይኩ። እግዚአብሔርም ሰማኝ፤ ምክንያቱም ይህ ሰው በብዙ የደምቢያ አድባራት ላይ ተሹሞ ሰዎች ጠልተውት ኖሮ ገደሉት። ሬሳው ከቤቱ ተገኘ፤ ገዳዩም ሳይገኝ ቀረ። ሹመቱንና ገንዘቡን ባዳ ወሰደው።

## ክፍል ዓሥራ ሶስት

ከክርስቶስ ልደት በ1645 ዓመት (B, 26v) በኢትዮጵያ ሀገሮች ሁሉ ታላቅ ረኀብ ገባ። ስለሕዝባችን ኀጢአትና በጓደኛ ፍቅር መጥፋት ምክንያት መቅሠፍቱ የጸና ሆነ። ምክንያቱም መጀመሪያ የንጉሥ ሱስንዮስንና የአቡነ እፎንስን ሃይማኖት የተቀበሉ ሃይማኖታቸውን ያልተቀበሉትን ወንድሞቻቸውን አሳደዷቸው፤ ገደሏቸውም። በኋላ ደግሞ የተሰደዱት (ቀን ሲወጣላቸው) ጠላቶቻቸውን ሰባት እጥፍ (አስ) ከፈሏቸው፤ ብዙዎችም ገደሉ። በዓይናቸው ፊት የእግዚአብሔር ፍርሃት እንደሌለ በሁሉም ዘንድ በግልጽ ታወቀ። የሰላምንም መንገድ አላወቋትም። ክርስቲያን የተባሉት በከንቱ ነው፤ ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ክርስቲያኖችን ከሁሉም አስቀድሞና ከሁሉም በላይ እርስ በርሳቸው ፍቅር እንዲኖራቸው ያዛቸዋል።[95] ግን ይኽ መፋቀር ክርስቲያን ከሚባሉት ማህል ፈጽሞ ጠፍቷል። ሁሉም በወንድሞቻቸው ላይ በደል ያደርሳሉ። እርስ በርሳቸውም እንደ እህል አበላል ይዋዋጣሉ።

ፋሲለደስ ንጉሣዊ አገዛዙን በጥሩ ዘዴና በጥበብ ጀምሮ ነበረ። ግን በጥሩነቱ አልጸና(በት)ም፤ አመፀኛ ንጉሥ ሆነ እንጂ፤ በዐመፅና ደም በማፍሰስ ጸና። ደግ የሠሩለትን፥ ግምቦችና ጥሩ ጥሩ ቤት የገነቡለትን፥ መንግሥቱን በጥበብ ሥራ ሁሉ ያሳመሩለትን ፈረንጆች (B, 27r) ጠላቸው፤ አሳደዳቸውም። በደግ ምትክ ክፉ ከፈላቸው። ይህ ፋሲለደስ በማንኛውም ሁሉ ክፉ ሠሪ ሆነ። ያለፍርድ ሰው ይገድላል፤ ዝሙትም አበዛ። ከሴቶቹ ጋራ ዝሙት ከሠራ በኋላ ገደላቸው። አመፀኛ ሠራዊቱን እየሰደደ ከተሞችና የደኻ ቤት ዘረፉ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለክፉ ሕዝብ ክፉ ንጉሥ ሰጥቷቸዋልና። በንጉሡና በሕዝቡ ኀጢአት የረኀብ መቅሠፍት ወረደ።

[95] ዮሐ 13፡34-35.

ከረኀብ ቀጥሎ ተስቦ ገባ።[96] ብዙዎች ሞቱ። ሌሎችም ፈሩ። (ፍርሃታቸው) ለድኅነት አልሆነም፤ ምክንያቱም በሞኝነታቸውና በጥላቻቸው ጸንተዋል። ግማሾቹ፥ "አቡነ እፎንስን ስላሳደዳችሁት የእግዚአብሔር መቅሰፍት መጣብን" አሉ። ሌሎቹ "መጀመሪያውኑ ትክክለኛዋን ሃይማኖት ስለከዳችኋትና ስላረከሳችኋት፥ ስለዚህ መቅሠፍት መጣ" አሉ። እርስ በርሳቸው ተለያዩ፥ ተነታረኩም። ኀደኛ መውደድን ስላፈረሱና እግዚአብሔር ለሰው አስተዳደር እንዲሆን ለፍጥረት ሁሉ ያቆመውን የእውነት ሥርዐት ስለተላለፉ መቅሠፍት እንደሚገባቸው አላወቁም።[97] (B, 27v) ስለ እንደዚህ የሰው ሕግ ወይም ስለ እንደዚህ ሃይማኖት የተፈጥሮን ሕግ ሻሩ። ኢሳይያስና ወንጌል ስለነሱ በጥሩው (እንዲህ) ብለዋል፤ "ይህ ሕዝብ በአፋቸው ያከብሩኛል፤ በልባቸው ግን ከኔ በረጅሙ ርቀዋል። ሰው የሠራውን ሥርዐት ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል።"[98] ደግሞ ዮሐንስ (እንዲህ) ብሏል፤ "ኀደኛን ጠልቶ በብርሃን ውስጥ አለሁ የሚል ውሸታም ነው፤ እስከዛሬ በጭለማ ውስጥ ነው ያለው። ኀደኛውን የሚወድ ግን በብርሃን ውስጥ ይኖራል። የሚያደናቅፈው በእሱ ዘንድ የለም። ኀደኛውን የሚጠላ ግን በጨለማ ውስጥ ይሄዳል፤ የሚሄድበትንም አያውቅም፤ ምክንያቱም ጭለማ ዓይኖቹን አሳውሯቸዋልና።"[99] ይህ ትንቢት በሀገራችን ሰዎች ላይ ተፈጽሟል። የሚሄዱበትን አያውቁም፤ ስለሃማኖቶቻቸው ይነታረካሉ፤ ምክንያቱም የሚያምኑትን አያውቁም፤ በጭለማ ውስጥም ይኖራሉ።

እኛ ግን በረኀቡ ጊዜ ወርቃችን ካለቀ በኋላ (B, 28r) ከብቶቻችንንና ልብሶቻችንን ሸጥን። ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰውና እንደሌሎች አልተራብንም፤ እንዲያውም እኛ በልተን የተራቡና የታመሙ አበላን፤ ረኀብና ተስቦ በሆነበት ሁለት ዓመትም አልተጎዳንም። "በክፉ ዘመናት አያፍሩም፤ በረኀብ ዘመን ይጠግባሉ"[100] ያለው በኛ ላይ ተፈጸመ። ቍጥር የሌለው ጥሩ ነገር የሠራልንን ግዚአብሔርን አመሰገንነው።

---

[96] በዚህ ዓመት ክበብ የሚባል ተስቦ ገብቶ ነበር።

[97] በሃይማኖት መለያየት መቅሠፍት የሚያመጣ "ኀጢአት" ከሆነ፥ ኀጢአት በዚህ ዘመን ብቻ የተፈጸመ አይደለም። በዚህ ፍልስፍናና እምነት ከሄድን፥ ዓለም ዘላለም በመቅሠፍት ሥር ልትኖር ነው።

[98] ኢሳ 29፡13፤ ማቴ 15፡8-9.

[99] 1 ዮሐ 2፡9-11.

[100] መዝ 36፡19.

## ክፍል ዓሥራ አራት

ከአንድ ዓመት በኋላ ጌታ ሀብቱ ሞተ። በጣም አዘንን፤ ከፍ ያለ ለቅሶም አለቀስንለት። ከመሞቱ በፊት ጠርቶን (እንዲህ) አለን፤ "እነሆ እኔ መሞቴ ነው፤ እግዚአብሔር ይጠብቃችሁ፤ ይባርካችሁም። አንተም ለልጆቼ አባታቸው ሁን።" ሁለት በሬና አንድ በቅሎ ሰጠኝ። ለሚስቴም ሁለት ላሞች ከነጥጃቻቸው ሰጣት። "ስለነፍሴ ጸልዩ" አለ። በእግዚአብሔር ሰላም ሞተ። የተባረከች ነፍሱን እሱ ያሳር(ፋት)። ከፍ ባለ ክብር ቀበርነው።

ወልደ ሚካኤል የሚባለው የበኩር ልጁ እንደ አባቱ ወደደኝ። ምክሬን ይሰማል። (B, 28v) ወለተ ጴጥሮስ የምትባል ሚስት አለችው፤ ፈንታዬ ትባላለች። በሀገሩ ክቡራን ማህል የተከበረች ናት። ምግባረ ጥሩ፥ በጓደኛ ፍቅርና በትሕትና የተሞላች ናት። እናት ልጆቿን እንደምትወድ ትወደናለች። ሁለቱ የሀብቱ ልጆች ተሰማና ምትኩ አደጉ፤ ዳዊት ደገሙ። ምትኩ በተጨማሪ ጽሕፈት፥ ሰዋስው፥ መጻሕፍት ዐወቀና ከኔ ጋራ በዕውቀትና በጠበቀ ፍቅር አንድ ሆነ። እሱ ምስጢሬን ሁሉ ያውቃል። ከሱ የደበቅሁት (አንዳችም) አልነበረም። ስለሱ ፍቅር፥ አጥብቆ ስለለመነኝ በኋላ ይኸንን በጥቂቱ ጻፍኩ።

## ክፍል ዓሥራ አምስት

ልጄም አደገ፤ መልከ መልካም ጎልማሳ ሆነ። እድሜው ሀያ ዓመት ግድም ሲሆን ባለማወቅ የወሲብ ፍላጎት ወደምታመለክት ጥፋት እንደሚያጠፋ አወቅሁ። በብዙው ገሠጽኩት። "ይኸ ሥራ እኮ አይገባም፤ ምክንያቱም ፈጣሪ ያቆመልንን ሥርዐት ያፈርሳል። ሚስት አግባና በተፈጥሮ ሥርዐት ኑር" አልኩት።[101] (እሱም) (B, 29r) "እሺ፥ ሚስት ስጠኝ" አለኝ። ፈለግሁና መድኃኒት የምትባል ቆንጆ ልጅ አገኘሁ፤ ከብሔረ ላምጌ የሆነ የከብት እረኞች አለቃ[102] ልጅ ናት። ልጄም ወደዳት፤ አባቷ ዓሥራ አምስት ላሞችና ልብሳ ልብስ ሰጣት። ለልጄ ሚስት ሆነችው። በአንድነት በፍቅር ኖርን።

---

[101]የ ዳ ኡርቢና ቅጂ፥ " አእመርኩ፡ ከመ፡ ውእቱ፡ ይኤብስ፡ በሥጋሁ፡ በከዊወ፡ ዘርእ፡ በእንተ፡ ጣዕም፡ ዘይረክብ፡ ቦቱ፡" (በሚያገኘው ደስታ ምክንያት፥ ዘር በማፍሰስ ጥፋት እንደሚያጠፋ ዐወቅሁ፡) ይላል። እንደ ዘፍጥረት 38፥9።

[102]የሰፈሩን ከብት በምንደኝነት የሚጠብቁ ይሆናሉ።

ከሁለት ዓመት በኋላ ወንድ ልጅ ወለደች፤ (ስሙን) "እግዚአብሔር ይባረክ" ስል "ይትባረክ" አልኩት። ደግሞ ወንድ ልጅ ወለደች፤ "ደስታዬ" አልኩት። ደግሞ ሴት ልጅ ወለደች፤ "ዕሴትየ"[103] አልኳት። ከደጎች (ነገሮቹ) ሁሉ ስላጠገበኝ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ።

ከሰዎች ጋራ ክርስቲያን እየመሰልኳቸው ኖርኩ። ግን በልቤ ውስጥ እሱ እንደገለጸልኝ፥ ከሁሉ ፈጣሪ፥ ከሁሉ ጠባቂ፥ ከእግዚአብሔር በቀር (ሌላ) አላምንም።

አስቤም፥ "ያልሆንኩትን አማኝ ስለምመስል በእግዚአብሔር ዘንድ ኀጢአት ይሆንብኝ ይሆንን? (እነሆ) ሰዎችን እንደዚህ እደልላቸዋለሁ" አልኩ። "ሰዎች እንዲደለሉ ይፈልጋሉ፤ እውነቱን ብገልጽላቸው ይሰድቡኝና ያሳድዱኛል እንጂ (ምክንያቴን) አይሰሙኝም። (B, 29v) በልቤ ያለውን መግለጽ ትልቅ ጥፋት ይሆናል እንጂ ጥቅም የለውም። ስለዚህ ከሰዎች ዘንድ እንደነሱ ሆኜ እኖራለሁ። በእግዚአብሔር ዘንድ (ደግሞ) እሱ እንደገለጸልኝ እኖራለሁ። ከኔ በኋላ የሚመጡ ያውቁኝ ዘንድ እስከ ሞቴ ድረስ እኔው ዘንድ የምደብቀውን ይኸንን ልጽፍ ወደድኩ። ከሞትኩ በኋላ አስተዋይና ተመራማሪ ሰው የተገኘ እንደሁ በሐሳቤ ላይ ሐሳቡን እንዲጨምር እለምነዋለሁ።

እነሆ ከዚህ በፊት ያልተተቸውን እኔ መተቸት ጀምሬያለሁ። የሀገራችን ሰዎች በእግዚአብሔር እርዳታ ጥበብ እንዲያገኙ፥ እውነትን ከማወቅ እንዲደርሱ፥ ውሸትን እንዳይተማመኑባት፥ እውነትን ዐውቀው ጓደኛቸውን እንዲያፈቅሩ፥ ከከንቱ ወደከንቱ እንዳይሄዱ፥ እንግዲህ እስከ ዛሬ እንዳደረጉት ስለ ሃይማኖታቸው እንዳይነታረኩ፥ እኔ የጀመርኩትን አንተ ፈጽመ(ው)። ይኸንንና ከዚህም የተሻለ የሚያስተውል ከተገኘና (B, 30r) ካስተማረው፥ ከጻፈውም እግዚአብሔር የልቡን ይስጠው። የሚወደውን ሁሉ ይፈጽምለት። እኔን እንዳጠገበኝ፥ ወጥመድ ከሌለበት ከደጋግ ነገሮቹ ያጥግበው። እኔን እስከዛሬ ድረስ እንዳስደሰተኝ፥ ደስተኛም እንዳደረገኝ በምድር ላይ ብፁዕ ያድርገው። በዚህ መጽሐፍ ምክንያት የሚሰድበኝ፥ እንዲያሻሽለው ለማስተዋል የማይፈልግ ግን እግዚአብሔር የሥራውን ይስጠው፤ አሜን።

[103] "ዋጋዬ" ማለት ነው።

## [መደምደሚያ]

ዘርአ ያዕቆብ፥ ማለት ወርቄ፥ በስድሳ ስምንት ዓመት ዕድሜው፥ ፋሲለደስ ሞቶ ዮሐንስ[104] ሲነግሥ፥ የጻፈው መጽሐፍ (እነሆ) ተፈጸመ። ዘርአ ያዕቆብ ይኽንን መጽሐፍ ከጻፈ በኋላ ፈጣሪያችንን እግዚአብሔርን እያፈቀረ፥ ቀንና ሌሊት እያመሰገነ፥ በጥሩ ሽምግልና ሃያ አምስት ዓመት ኖረ። በጣም የተከበረ ሆነ። የልጁን የልጅ ልጆች አየ። ልጁ ሀብቱ ከሚስቱ ከመድኃኒት አምስ ወንድ፥ አራት ሴት ወለደ። የዘርአ ያዕቆብ፥ ማለት የወርቄ፥ ጉዳት የሌለበት ጠቅላላ ዘመኑ ዘጠና ሶስት ዓመት ሆኖ፥ (B, 30v) በፈጣሪያችን ታላቅ ተስፋ ኖሮት ሞተ። ሚስቱም ከአንድ ዓመት በኋላ ሞታ ከባሏ አገጠብ ተቀበረች። እግዚአብሔር ነፍሳቸውን ዘላለም በሰላም ይቀበል።

ልጁና የልጅ ልጆች በሀገራችን የተበከሩ ሆኑ። በአባታቸው በረከትም ተባረኩ። ከብቶቻቸው ከብዛታቸው የተነሣ ቤታቸው አልበቃቸውም። ግማሾቹ ወደእናታቸው ዘመዶች ወደቆላ ሄደው እዚያ ኖሩ።

እነሆ እግዚአብሔርን የሚፈራ እንደዚህ ይባረካል። እግዚአብሔር በአባቴ በሀብቱ በረከትና በመምህሬ በዘርአ ያዕቆብ በረከት ይባርከን፤ እኔም በጣም ሽማግሌ ሆኛለሁ። በእድሜ ገፍቼ ከመርሳት ደርሻለሁ። እውነተኛ የሆነ ሲወድቅ አላየሁም፤ ዘሩም በእህል (እጦት) አይቸገርም፤ ዘላለም በበረከት ውስጥ ይኖራል።

እኔም፥ ምትኩ የምባለው ወልደ ሕይወት፥ (የመምህሬን) መልካም መጨረሻውን ታውቁ ዘንድ በመምህሬ መጽሐፍ ላይ ይችን ትንሽ (አንቀጽ) ጨመርኩ። ስለጥበቤ ደግሞ እግዚአብሔር ያስገነዘበኝ (እነሆ )፤ [105]

[ዘርአ ያዕቆብ አምሳ ዘጠኝ ዓመት ስላስተማረኝ ለኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ ዕውቀትና ተግሣጽ እንዲሆናቸው እነሆ ሌላ መጽሐፍ ጽፌያለሁ። እግዚአብሔር ልቡና፥ ጥበብ፥ ፍቅር ይስጣቸው፤ ለዘለዓለም ይባርካቸው፤ አሜን። ይቺ መጽሐፍ ተፈጸመ።][106]

---

[104]አእላፍ ሰገድ፥ ጻድቁ ዮሐንስ (1660-1674).

[105]ምትኩ/ወልደ ሕይወት የመምህሩን የወርቄን (የዘርአ ያእቆብን) ድርሰት በዚህ ያቆምና የራሱን ድርሰት ያስከትላል።

[106]ይህን አንቀጽ በ**ሐተታ ዘዘርአ ያዕቆብ** ላይ የጨመረው ዳ ኡርቢኖ ነው። ፊደል አጻጻፉና የሰዋስዉ ብልሹነትም ይመሰክራሉ።

# ዋቢ ምንጭ


አምሳሉ አክሊሉ (ዶክተር)፥ ዘርዓ ያዕቆብ ፈላስፋው፥ ታሪክ *Tarik, gazette d'information archeology*, no. 1 (1963), pp. 11-13.

Alemayyehu Moges, *Ḥatäta Zäzär'a Ya'əqob, Ethiopian Philosopher*, a thesis presented at Haile Selassie I University 1961 EC (1968 AD.).

Rossini, Carlo Conti, "Notice sur les manuscrits éthiopians de la collection d'Abbadie," *Journal Asiatique*, ser. 10, vol. 20 (1913), pp. 23-24.

——, "Lo Hatatā Zar'a Yāʿqob e il Padre Giuso da Urbino" *Rendiconti della Reale Accademia dei Lincei*, ser. v, vol. xxix (1920), pp. 213-23.

d'Abbadie, Antoine, *Catalogue raisonné de manuscrits éthiopians appurtenant à Antoine d'Abbadie*, Paris 1859, p. 212.

Dawit Worku Kidane, *The Ethics of Zär'a Ya'əqob. A reply to the historical and religious violence in the seventeenth century Ethiopia (Testi Gregoriana Serie Filosofia 30)*, Rome 2012.

Littmann, Enno, *Zar'a Jacob, ein einsamer Denker in Abessinien, mit einer Einleitung von Benno Erdman*, Berlin 1916.

——, *Philosophi Abessini*, *Corpus Scriptorum Christianorum Orientaliun*, script. aeth. textus series prima tomus xxxi, Paris 1909, reprint vol. 18, script. aeth. t. 1 (1962).

Luam Tesfalidet, *Rezeptionsgeschichte der Ḥatäta Zär'a Ya'əqobs und Wäldä Ḥəywät*, Universität Hamburg, Hamburg 2007.

Mittwoch, Eugen, "Die amharische Version der Soirée de Carthage mit einer Einleitung: Die angeblichen abessinischen Philosophen des 17. Jahrhunderts," *Abessinische Studien*, Heft II, Berlin and Leipzig 1934.

Sumner, Claude, *Ethiopian Philosophy, Vol. II, The Treatise of Zâr'a Ya'eqob and of Wäldä Heywot. Text and authorship*. Addis Ababa University Press, 1976; *Vol. III: The Treatise of Zâr'a Ya'eqob and of Wäldä Heywot. An Analysis*, Addis Ababa University Press, 1981; idem., *Classical Ethiopian Philosophy*, Adey Publishing Company, Los Angeles 1994.

Turayev, Boris, "Hatata Zar'a Ya'èqob. Izledovaniye Zarya Yakob. Ispoved abissinskavo Svobodnavo myslitelya XVII veka," *Imperatorskoye Russkoye Arkheologicheskoe Obshchestvo. Zapisi Vostochnavo Otdeleniya*, vol. 16 (1905), pp. 1-16.

# መጠቆም

(1. ኅ = ኅዳግ፤ 2. ቃሉ በተሰጠው ገጽ ላይ ተደጋግሞ ሊመጣ ይችላል።)

ሀብተ እግዚአብሔር፡ 36፥ 39
ሀብቱ፡ 36፥ 37፥ 38፥ 39፥ 42፥ 44
ህንዶች፡ 25
ሉአም ተስፋ ልደት፡ 7
ላምጌ (ብሔረ)፡ 42
ላቲን፡ 6
መሐመድ፡ 22፥ 24፤ ኅ 88
መርጨት፡ 20
መነኮሳት፡ 36
መነኲሴ፡ 16፥ 27፥ 38
መድኃኒት፡ 42፥ 44
ሙሴ፡ 21፥ 23፥ 25፤ ኅ 37፥ 39፥ 44፥ 88
ሚትሮኽ፡ 7፥ 10
ምትኩ፡ 37፥ 42፥ 44፤ ኅ 105
ምንኲስና፡ 22፥ 27፥ 38
ረኀብ፡ 15፥ 27፥ 40፥ 41
ሮማዊ፡ 6፥ 7
ሰሎሞን፡ 20፥ 28፥ 31
ሱስንዮስ (አፄ)፡ 6፥ 8፥ 9፥ 10፥ 14፥ 16፥ 36፥ 39፥ 40
ሲኖዶስ፡ ኅ 48
ሸዋ፡ 16
ቁርአን፡ ኅ 49
በዓለ ኃምሳ፡ 25
በጌምድሬ፡ 9
በጌምድር፡ 36
ባሕረ ሐሳብ፡ 7፥ 10፥ 11፥ 12
ቦሪስ ቱራኢየቭ፡ 10
ተሰማ፡ 37፥ 42
ተስቦ፡ 41፤ ኅ 96
ተከዚ፡ 15
ተዋሕዶዎች፡ ኅ 13
ቱራኢየቭ፡ 10
ቶማስ አኩይናስ (ቅዱስ)፡ 10

ኂሩት፡ 38
አልፎንስ (አባ፥ ጳጳስ)፡ 6
አማርኛ፡ 6፥ 7፥ 11
አምሐራ፡ 16፥ 36
አሰፋ ገብረ ማርያም ተሰማ፡ 7
አስማት፡ 20
አንቷን ዳ'አባዲ፡ 5
አእላፍ ሰገድ/ዮሐንስ (አፄ)፡ 5፤ ኅ 104
አክሱማዊት፡ 14
አክሱም፡ 6፥ 8፥ 9፥ 10፥ 13፥ 15፥ 36፥ 37፥ 38፥ 39
አይሁድ፡ 18፥ 19፥ 25፥
ኢሳይያስ (ነቢይ)፡ 41
ኢትዮጵያ፡ 5፥ 6፥ 7፥ 8፥ 9፥ 10፥ 15፥ 36፥ 40፥ 44፤ ኅ 90
ኢትዮጵያዊ/ውያን፡ 5፥ 6፥ 7፥ 8፥ 10፥ 11፥ 19
ኢትዮጵያዊነት፡ 10
ኢየሱስ ክርስቶስ፡ 40፤ ኅ 88
ኢጣሊያዊ፡ 7
ኤኖ ሊትማን፡ 9
እስላም/እስላሞች፡ 18፥ 19፥ 20፥ 22፥ 24፥ 25፥ 26
እንግሊዝኛ፡ 7
እንፍራዝ፡ 9፥ 36፥ 39
እፎንስ (ጳጳስ)፡ 14፥ 39፥ 40፥ 41
ኦሪት፡ 22፥ 29
ኦርቶዶክሳዊ/ኦርቶዶክሶች፡ 6፥ 10፤ ኅ 14፥ 41
ኦርቶዶክስ፡ 9፥ 10
ኦይገን ሚትቮኽ፡ 6
ካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ፡ 6
ካቶሊካዊ/ካቶሊኮች፡ 6፥ 8፥ 9፥ 10፥ 11፤ ኅ 10፥ 12፥ 41
ካቶሊክ፡ 5፥ 6፥ 9፥ 10
ክላውድ ሳምነር፡ 10
ክርስቲያን/ኖች፡ 6፥ 10፥ 22፥ 23፥ 24፥ 25፥ 26፥ 40፥ 43
ክርስትና፡ 6፥ 8፥ 14
ክርስቶስ፡ 6፥ 7፥ 12፥ 13፥ 39፥ 40፤ ኅ 88
ክበብ (ተስቦ)፡ ኅ 96
ኮንቲ ሮሲኒ፡ 6፥ 7
ኮከብ ቈጠራ፡ 20
ወለተ ጴጥሮስ፡ 42
ወልደ ሕይወት፡ 5፥ 37፥ 44፤ ኅ 105
ወልደ ሚካኤል፡ 37፥ 42
ወልደ ዮሐንስ፡ 9፥ 15፥ 32፥ 39
ወልደ ገብርኤል፡ 37
ወልደ ጊዮርጊስ፡ 11

ወልደ ፋሲለደስ፡ 11፤ ኀ 90
ወርቁ፡ 5፥ 6፥ 7፥ 8፥ 9፥ 10፥ 14፥ 44፤ ኀ 105
ወንጌል፡ 23፥ 24፥ 26፥ 29፥ 41
ዕሴትየ፡ 43
ዘርአ ያዕቆብ፡ 5፥ 6፥ 7፥ 8፥ 9፥ 10፥ 11፥ 12፥ 13፥ 14፥ 44፤ ኀ105
ዝዙዊት፡ 6
ያዕቆብ (አፄ)፡ 13
ዮሐንስ/አእላፍ ሰገድ (አፄ)፡ 5፥ 44፤ ኀ 104
ዮሐንስ (ወንጌላዊ)፡ 41
ይትባረክ፡ 43
ደምቢያ፡ 5፥ 8፥ 9፥ 40
ደስታ ተክለ ወልድ (አለቃ)፡ 6፥ 7
ደስታዬ፡ 43
ደብረ ሲና፡ 21
ደብረ ታቦር፡ 5
ደንቀዝ፡ 8
ዳ ኡርቢኖ (ፓድሬ ጁስቶ)፡ 5፥ 6፥ 7፥ 8፥ 10፥ 11፥ 12፤ ኀ 101፥ 106
ዳዊት (መዝሙረ)፡ 9፥ 10፥ 14፥ 15፥ 16፥ 17፥ 18፥ 19፥ 25፥ 32፥ 33፥ 34፥ 37፥ 39፥ 40፥ 42፤ ኀ 81
ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ፡ 5፥ 6፥ 11
ጋብቻ፡ 22፥ 23፥ 27፥ 38
ጋኔን መሳብ፡ 20
ግራኝ፡ 10
ግብጽ፡ 21
ግብጻዊ/ውያን፡ 8፥ 15፥ 16፥ 36
ግብጾች፡ 39
ግዕዝ፡ 5፥ 6፥ 11
ጎንደሬ፡ 9፥ 11
ጐዣም፡ 36
ጠንቋዮች፡ 20
ጥንቈላ፡ 20
ጦም፡ 25
ጴጥሮስ (ሐዋርያ)፡ 16
ጸሎት፡ 10፥ 16፥ 30፥ 31፥ 32፥ 33፥ 34
ጾም፡ 24፥ 25፥ 27
ፈረንጅ/ጆች፡ 5፥ 6፥ 8፥ 9፥ 14፥ 15፥ 16፥ 18፥ 19፥ 25፥ 32፥ 36፥ 39፥ 40
ፈንታዬ፡ 42
ፋል፡ 20
ፋሲለደስ (ቅዱስ)፡ 11
ፋሲለደስ (አፄ)፡ 9፥ 10፥ 11፥ 36፥ 39፥ 40፥ 44፤ ኀ 90

ፋሲል፡ (አፄ)፡ 11፤ ኅ 90
ፋሲካ፡ 25
ፓሪስ፡ 5፥ 7፥ 9

d'Abbadie, Antoine: 5
da Urbino, Padre Giusto: 5
Littmann, Enno: 9
Mendez, Alfonso: n. (ኅ)11
Mittwoch, Eugen: 6
*One Thousand and One Nights:* 10
Sumner, Claude: 10
Thomas Aquinas: 10
Turayev, Boris: 10

